## የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን

Ethiopian Capital Market Authority

# የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፣ የተዛማጅ ውሎች እና ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያዎች የፈቃድ አሰጣጥ፣ የአሰራር እና የቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 1009/2016

ሐምሌ 2016

ማውጫ


መግቢያ ..... 4
ክፍል አንድ ..... 5
ጠቅላላ ድንጋጌዎች ..... 5
1. አጭር ርዕስ ..... 5
2. ትርጓሜ ..... 5
3. የተፈፃሚነት ወሰን ..... 6
4. ፈቃድ ለማውጣት ስለሚቀርብ ማመልከቻ ..... 6
5. ለማመልከቻ የሚቀርቡ ሰነዶች፡- ..... 7
6. ስለፈቃድ እና ገደቦች ..... 8
7. ስለማመልከቻ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት ..... 8
8. ፈቃድ ስለመከልከል ..... 9
9. ፈቃድ ስለማደስ፣ ስለማገድ እና ስለመሰረዝ ..... 10
10. ስለክፍያዎች ..... 10
ክፍል ሁለት ..... 11
የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ..... 11
11. ገበያውን ራሱን በራሱ ለሚቆጣጠር ድርጅት የሚያበቁ መስፈርቶች ..... 11
12. ስለገበያ ፈቃድ መስፈርቶች ..... 11
13. ስለዝቅተኛ የካፒታል መስፈርቶች ..... 12
14. የገበያ ፈቃድ ..... 13
15. በገበያው ላይ ስለተጣሉ ገደቦች ..... 13
16. ስለገበያው አደረጃጀት ..... 13
17. ስለዳይሬክተሮች ቦርድ ..... 13
18. ስለአስተዳደር መዋቅር ..... 14
19. ስለዋና ስራ አሥፈፃሚ ..... 14
20. ስለገበያው ከፍተኛ ባለሙያዎች ..... 15
21. የሰው ኃይል እና የቴክኒክ ክህሎት ..... 15
22. ስለስጋት እና ሕግ ማስከበር ..... 15
23. ሥራን በሦስተኛ ወገን ስለማሰራት ..... 16
24. የግብይት መድረኮች ወይም ሥርዓቶች ጠቅላላ መስፈርቶች ..... 18
25. የግብይት መድረክ ወይም ሥርዓት ብቃት ..... 18
26. ስለግብይት መድረኮች ወይም ሥርዓቶች አቅም ..... 19
27. የግብይት መድረክ ወይም ሥርዓት ለመጠቀም የሚቻልበት ሁኔታዎች ..... 20
28. ሥርዓት፣ ቁጥጥር እና የአስተዳደር መዋቅር ..... 21
29. ሥርዓት ያልተከተሉ የግብይት ሁኔታዎችን ስለመከላከል ..... 22
30. የግብይት መድረክ ወይም ሥርዓት በትክክል መሥራትን ስለመፈተሽ ..... 24
31. የግብይት መድረክ ወይም ሥርዓት ላይ የሚደረግ ቀጣይነት ያለው ክትትል ..... 24

32. መዋዠቅን የማስተዳደሪያ መንገዶች ....25
33. ቅድመ-ግብይትና ድህረ-ግብይት ቁጥጥር ....26
34. አነስተኛ የዋጋ እንቅስቃሴ መጠን ....26
35. የግብይት ሰዓቶችን ማቀናጀት ....27
36. ገበያ ስለመክፈት ....27
37. ከግብይት መድረኮች ጋር ተያያዥነት ያላቸው የክፍያ መርሆዎች ....28
38. ስለዳታ ጥበቃ ....28
39. ስለቴክኖሎጂ እና ደህንነት ....28
40. ስለንግድ ቀጣይነት ....29
41. ስለአባላት ግምገማ ....30
42. ስለቴክኒካዊ እና ተግባራዊ የተስማሚነት ፍተሻ ....31
43. ስለግብይት ሥርዓት፣ ስትራቴጂ ወይም የስልተ-ቀመር ሙከራ ....32
44. የገበያው ውስጠ-ደንቦች - ጠቅላላ ....33
45. ስለአባልነት ውስጠ-ደንቦች ....33
46. የግብይት መድረኩን ወይም የሥርዓቱን ተደራሽነት የሚመለከቱ ውስጠ-ደንቦች ....33
47. በቀጥታ በኤልክትሮኒክ መሳሪያ ስለመሳተፍ ....34
48. ስለግብይት ውስጠ-ደንቦች ....35
49. ስለኮሎኬሽን ....35
50. ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ ወይም ቅበላ የሚመለከቱ ውስጠ-ደንቦች ....35
51. የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ከምዝገባ ወይም ከግብይት ስለመታገድ እና መነሳት ....36
52. ስለክትትል እና ቅኝት ....36
53. ስለምርመራ እና የዲሲፕሊን እርምጃ ....37
54. ቀጣይነት ስላላቸው ግዴታዎች ....37
55. ለባለሥልጣኑ ሪፖርት እና እገዛ ስለማድረግ ....38
56. የሂሳብ ሪፖርቶችን ለባለሥልጣኑ ስለማቅረብ ....39
ክፍል ሦስት ....40
ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ....40
57. ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ፈቃድ መስፈርቶች ....40
58. ስለዝቅተኛ የተከፈለ ካፒታል መስፈርት ....41
59. ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ፈቃድ ....42
60. ስለተመዘገቡ ሰዎች ....42
61. የዋጋ ተመን ሥርዓት ....43
62. ስለክፍያ ማጣራትና መፈጸም ....44
63. ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ለግብይት ብቁ የሆኑ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ....44
64. ስለውሉች ....45
65. ከዋጋ ተመን ሥርዓቱ በፊት ስለሚፈለጉ መረጃዎች ....45
66. ግብይቶችን ይፋ ስለማድረግ ....45

67. ክፍያዎችን ይፋ ስለማድረግ ....46
68. ቀጣይነት ስላላቸው ግዴታዎች ....46
69. ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ፈቃድ ስለመሰረዝ ወይም መመለስ ....46
ክፍል አራት ....48
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ....48
70. መስፈርቶችን በጊዜያዊነት ስለመተው ወይም መቀነስ ....48
71. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው መመርያዎች ....48
72. መመሪያው የሚጸናበት ቀን ....48

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን

**<u>መግቢያ</u>**

የካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013 የኢትዮጵያ የሰነደ መዓለ ንዋዮች ገበያ በአክሲዮን ማህበር መልክ እንደሚቋቋም እና በሚቋቋምበት ጊዜ አሰራሩን በተመለከተ ባለሥልጣኑ በመመሪያ እንዲያወጣ ሥልጣን የተሰጠው በመሆኑ፤

የሌሎች የሰነደ መዓለ ንዋዮች ገበያዎች፣ የተዛማጅ ውሎች ገበያዎች እና ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያዎች የፈቃድ እና የአሰራር መስፈርቶችን መመሪያ በማውጣት መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፤

የኢንቨስተሮችን ጥቅም ለመጠበቅ፣ የገበያውን ተአማኒነት ለማረጋገጥ እና የኢትዮጵያን የካፒታል ገበያ እድገት ለማበረታታት ሥርዓት ያለው፣ ፍትሃዊ፣ ቀልጣፋ እና ግልፅ ገበያ እንዲኖር ለማስቻል የቁጥጥር ማዕቀፍ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ይህ መመሪያ በካፒታል ገበያ አዋጁ ቁጥር 1248/2013 አንቀፅ 31(5)፣ አንቀጽ 32(2) እና አንቀጽ 108 (2) መሠረት ወጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፣የተዛማጅ ውሎች እና ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያዎች የፈቃድ አሰጣጥ፣ የአሰራር እና የቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 1009/2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1/ "አዋጅ" ማለት የካፒታል ገበያ አዋጅ ቁ.1248/2013 ነው፡፡

2/ "ስልተ-ቀመራዊ ግብይት" ማለት በኮምፒዩተር ሥርዓቶች የሚደረግ ማንኛውም አይነት በቴክኖሎጂ የተደገፈ ግብይት ሲሆን ለተለያዩ የገበያ መረጃዎች ምላሽ በመስጠት የተወሰኑ እርምጃዎችን እንዲወስድ ፕሮግራም የተደረገ ነው፡፡

3/ "ኃላፊነትን ስለመወጣት የሚቀርብ አመታዊ ሪፖርት" ማለት በዚህ መመሪያ መሠረት ፈቃድ የተሰጠው አካል በዚህ መመሪያ የተጣሉ ኃላፊነቶችን በሙሉ መወጣቱን የሚያካትት ለባለሥልጣኑ የሚያቀርበው የማረጋገጫ ሪፖርት ነው፡፡

4/ "አመልካች" ማለት  የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ፣ የተዛማጅ ውሎች ገበያ ወይም ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ለማቋቋም ወይም ለማካሄድ ፈቃድ የጠየቀ ተቋም ነው፡፡

5/ "ስልጣን የተሰጠው ማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 54 መሠረት የሰነደ ሙዓለ ንዋይ የማከማቸት እና የክፍያ እና የማጣራት አገልግሎት እንዲሰራ ስልጣን የተሰጠው አካል ነው፡፡

6/ "ባለሥልጣን" ማለት በአዋጁ  የተቋቋመ የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ነው፡፡

7/ "የስራ ቀናት" ማለት ከቅዳሜ፣ እሁድ እና በኢትዮጵያ የቀን አቆጣጠር መሰረት የህዝብ በዓላት ተብለው ከተገለጹት ቀናት ውጭ ያሉት ናቸው፡፡

8/ "የካላንደር ቀናት" ማለት በኢትዮጵያ የቀን አቆጣጠር መሰረት ቅዳሜን፣ እሁድን፣ የህዝብ በዓላትንና በመንግስት አዋጅ መሰረት ስራ ዝግ የሚሆንባቸውን ቀናት ጨምሮ ተከታታይነት ያላቸው ቀናት ናቸው፤

9/ "የኮሎኬሽን"  ማለት የቴክኖሎጂ የግብይት ሥርዓቶችን ወይም አደረጃጀቶችን ከግብይቱ መድረክ ወይም ስርዓት አቅራቢያ ወይም አጠገብ ለማስቀመጥ የሚደረግ ስምምነት ነው፡፡

10/ "በቀጥታ በኤልክትሮኒክ መሳሪያ መሳተፍ" ማለት ማንኛውም ከሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ጋር የሚደረግ የኤሌክትሮኒክ ግንኙነት አይነት ሆኖ የአንድ የገበያው አባል ደንበኞች በውስን የአባሉ ጣልቃ ገብነት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለመግዛት ወይም ለመሸጥ ትዕዛዞችን ማስቀመጥ የሚፈቅዱ አገልግሎቶች ናቸው፡፡

11/ "ገንዘብ አከል ሀብት" ማለት ጥሬ ገንዘብ እና ጉልህ የዋጋ ለውጥ ሳይኖር ወደ ጥሬ ገንዘብ ሊለወጥ በሚችል የገንዘብ ሰነዶች መልኩ የሚገኝ ሃብት ነው፡፡

12/ "የተመዘገበ ሰው" ማለት ለዚህ መመሪያ ክፍል ሦስት ዓላማ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ የዋጋ ተመን ሥርዓትን ለመጠቀም ብቁ የሆነ ወይም በባለሥልጣኑ ይሁንታ ያገኘ ሰው ነው፡፡

13/ "ድጋፍ ያለው ተሳትፎ" ማለት በገበያው በቀጥታ ኤሌክትሮኒክ መሳሪያ መሳተፍ ውስጠ-ደንብ መሠረት የተሰጠ የገበያው የግብይት መድረክ ወይም ሥርዓት የመሳተፍ እድል ነው፡፡

14/ "የዋጋ ተመን ሥርዓት" ማለት ማንኛውም በተገበያዮች መካከል የሚኖር የዋጋ አሰጣጥ ስርዓት ወይም ማንኛውም የህትመት ውጤት፣ የአሰራር ሂደቶች ጥምረት፣ የኤሌክትሮኒክ የመገናኛ መረብ ወይም ሌላ መሣሪያ ወይም እነዚህ ዘዴዎችን በጋራ በማቀናጀት የሚፈጠር ነው፡፡ ይህን ስርዓት በመጠቀም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አከናዋኞች ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ደላላዎች በጋራ ወይም በተናጠል አንድ የተጠቀሰ ዋጋ በሌሎች እንዲታወቅ ወይም ለራስ ወይም ለደንበኞቻቸው እንዲገዙ ወይም እንዲሸጡ ግብዣ የሚቀርብበት ነው፡፡

15/ "መቆጣጠሪያ" ማለት በኤሌክትሮኒክስ ግንኙነት ሥርዓት ላይ ያለውን የዳታ ፍሰት የማስተዳደር ሂደት ነው፡፡

16/ "አነስተኛ የዋጋ እንቅስቃሴ መጠን" ማለት አነስተኛ የዋጋ ለውጥ መጠን ሆኖ በገበያው በሚገበያዩ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ከፍ ወይም ዝቅ የሚሉበት የዋጋ ለውጥ ነው፡፡

17/ "መዋዠቅ" ማለት በገበያ ውስጥ ወይም በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ወይም በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ስብስብ ዋጋ ላይ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የሚከሰት የዋጋ መለዋወጥ ነው፡፡

18/ በአዋጁ ትርጓሜ የተሰጣቸው ቃላትና ሐረጋት ለዚህ መመሪያም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

19/ በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ፣ የተዛማጅ ውሎች ገበያ ወይም ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ አገልግሎት ለማቋቋም ወይም ለማከናወን በሚፈልጉ አካላት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 4. ፈቃድ ለማውጣት ስለሚቀርብ ማመልከቻ

1/ በዚህ መመሪያ መሰረት የፈቃድ ማመልከቻው በአዋጁና በዚህ መመሪያ ላይ የተቀመጡት መስፈርቶች እና ሁኔታዎች መሟላታቸውን ባለሥልጣኑ እንዲያረጋግጥ ለማስቻል አስፈላጊ መረጃዎችን ያካተተ መሆን አለበት፡፡

2/ ማንኛውም ማመልከቻ በአንቀጽ 5 ስር በተጠቀሱ ሰነዶች የተደገፈ ሆኖ የሚከተሉትን የሚገልጽ መሆን አለበት፡-

ሀ) ፈቃድ የተጠየቀው ለሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ፣ ለተዛማጅ ውሎች ገበያ ወይም ላልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ መሆኑን፣ እና

ለ) ለግብይት የታቀዱትን የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አይነት እና በነዚህ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ለመገበያየት መብት የሚኖራቸውን የኢንቨስተሮች መደብ፡፡

5. **ለማመልከቻ የሚቀርቡ ሰነዶች፡-**

የሚፈለጉት ሰነዶች የሚከተሉትን መረጃዎች ማካተት አለባቸው፡-

1/ ጠቅላላ መረጃዎች፡-

ሀ) የአመልካቹ ሕጋዊ ስም፤

ለ) የአመልካቹ እና የሥራው የተመዘገበ አድራሻ፤እና

ሐ) ስለ አመልካቹ ፈራሚውን የሚመለከት መረጃ፡፡

2/ የድርጅት መረጃ፡-

ሀ) አመልካቹ የአክሲዮን ማህበር ስለመሆኑ የሚቀርብ ማረጋገጫ፤

ለ) የተመዘገበበት ቀንና ቦታ፤

ሐ) የመመስረቻ ፅሑፍ ወይም መተዳደሪያ ደንብ፣ የምዝገባ ምስክር ወረቀት፤

መ) የንግድ ምዝገባ እና የንግድ ሥራ ፈቃድ ቁጥር (አግባብነት ሲኖረው)፤እና

ሠ) የግብር መክፈያ መለያ ቁጥር፡፡

3/ የአደረጃጀት መረጃዎች፡-

ሀ) የኩባንያው ወይም የድርጅቱ መዋቅር፤

ለ) የአመልካቹ ባለቤትነት ወይም ባለአክሲዮኖች ዝርዝር፤ እና

ሐ) የእጩ ከፍተኛ አመራር እና ዳሬክተሮች ቦርድ ዝርዝር፡፡

4/ የግብይት ሥራ አሰራር እና እንቅስቃሴ መረጃዎች፡-

ሀ) የአመልካቹ ወቅታዊ እና የታቀደ ሥራ እና ተግባራት፤

ለ) በሚቀጥሉት ከ3 እስከ 10 ዓመታት ውስጥ የግብይት ሥራውን ለማከናወን እና ለማስፋፋት በአመልካቹ የታቀዱ እቅዶች፤እና

ሐ) ለግብይት የታሰቡ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ አይነት፣እንዲገበያዩ የታቀዱ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች እና

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን

በእነዚህ ሰነዶች እንዲገበያዩ የተፈቀደላቸው ኢንቨስተሮች መደብ ዝርዝር፡፡

5/ የተጠየቀው ፈቃድ መረጃ፡-

ሀ) በዚህ መመሪያ ውስጥ በተገለጸው መሠረት የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያን፣ የተዛማጅ ውሎች ገበያን ወይም ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያን ፈቃድ መስፈርቶችን መከበራቸውን ለማረጋገጥ አስፈላጊው መረጃ፤ እና

ለ) ማመልከቻው የቀረበው ፈቃድ በተሠጠው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ስም አዲስ ወይም ተጨማሪ ሥራ ለመስራት ወይም አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ ለማግኘት ከሆነ በመመሪያው ከሚጠየቁ መስፈርቶች አንፃር ለመገምገም እንዲያስችል ስለ አገልግሎቱና ተግባራቱ ሁሉንም ተዛማጅ ዝርዝሮች ማቅረብ፤

ይኖርበታል፡፡

6/ ሌሎች በባለሥልጣኑ የሚፈለጉ ሰነዶችን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

6. <u>**ስለፈቃድ እና ገደቦች**</u>

1/ የገበያ ፈቃድ የተሰጠው አመልካች በማመልከቻው በተገለጸው እና በባለሥልጣኑ በጸደቀው መሠረት የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ፣ የተዛማጅ ውሎች ገበያ ወይም ሁለቱንም እንዲያከናውን ይፈቀድለታል፡፡

2/ የገበያ ፈቃድ የተሰጠው አመልካች በዚህ መመሪያ መሰረት ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ፈቃድ ወይም ባለሥልጣኑ በሚያወጣው አግባብነት ባለው መመሪያ መሠረት በባለሥልጣኑ ለሚሰጥ ሌላ ፈቃድ ማመልከት ይችላል፡፡

3/ በአዋጁ ላይ በተገለጸው መሠረት ፈቃድ ካለው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ውጪ በሌላ ሰው የተገኘ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ፈቃድ በርዕሱ ወይም በንግድ ሥራው ውስጥ "ገበያ" የሚሉትን ቃላት መጠቀም አይፈቀድለትም፡፡

4/ በዚህ መመሪያ ማንኛውም ድንጋጌ ቢኖርም ባለሥልጣኑ የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ የተቀመጡ መስፈርቶችን ሲያሟላ በአዋጁ አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት የገበያ ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

5/ በዚህ መመሪያ ማንኛውም ድንጋጌ ቢኖርም ባለሥልጣኑ ለሌሎች አመልካቾች ሁሉ የገበያ ፈቃድ ወይም ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ፈቃድ የሚሰጠው በአዋጁ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የመወሰን ስልጣኑን በመጠቀም የገበያውን ዕድገት እና የቁጥጥር አቅሙን ግምገማ መሠረት በማድረግ፣ እና በአዋጁ አንቀጽ 5 የተቀመጡትን ዓላማዎች ለማሳካት ይሆናል፡፡

6/ በዚህ መመሪያ ውስጥ ያሉት መስፈርቶች ለኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ እና ሌሎች በዚህ መመሪያ መሰረት ፈቃድ ላገኙ አመልካቾች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

7. <u>**ስለማመልከቻ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት**</u>

1/ ሁሉም ማመልከቻዎች በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች መሠረት መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን

2/ ሁሉም ማመልከቻዎች እና አባሪ ሰነዶች በእንግሊዘኛ ወይም በአማርኛ ቋንቋዎች ለባለሥልጣኑ መቅረብ አለባቸው። ከማመልከቻው ጋር አባሪ ሆኖ የሚቀርብ ማንኛውም መረጃ ወይም ሰነድ በሌላ ቋንቋ ከሆነ ወደ እንግሊዘኛ ወይም አማርኛ ተተረጉሞ ከተረጋገጠ ቅጂ ጋር መቅረብ ይኖርበታል።

3/ ሁሉም የማመልከቻ መረጃዎች እና ሰነዶች ወይም የእነዚሁ ቅጂዎች በኤሌክትሮኒክ አይነት መቅረብ ያለባቸው ሆኖ፣ ግልጽ እና በቀላሉ ሊነበቡ የሚችሉ መሆን አለባቸው።

4/ አስቀድሞ ለባለሥልጣኑ በተሰጠ መረጃ ላይ የሚቀርብ ማንኛውም ጉልህ ለውጥ ካለ እና ለውጡ አመልካቹ በአዋጁ እና በመመሪያው መሠረት ተገቢውን መስፈርት ማሟላቱን ለማረጋገጥ የሚረዳ ከሆነ ለባለሥልጣኑ ወዲያውኑ መቅረብ አለበት።

5/ ባለሥልጣኑ ማመልከቻውን በተቀበለ በሰላሳ (30) ተከታታይ የካላንደር ቀናት ውስጥ ማመልከቻው የተሟላ መሆን አለመሆኑን ለአመልካቹ ማሳወቅ አለበት።

6/ የተጠየቀው የማመልከቻ ክፍያ የተከፈለ ቢሆንም በዚህ መመሪያ መሠረት የቀረበ የፈቃድ ማመልከቻ አመልካቹ ባለሥልጣኑን በአግባቡ ሳያሳውቅና ሳይፈቀድለት ለስልሳ (60) ተከታታይ የካላንደር ቀናት የፈቃድ ማመልከቻውን ሂደት ካልቀጠለበት ወይም ችላ ካለ ባለሥልጣኑ ሂደቱን ሊያቋርጠው ይችላል።

7/ የተሟላ ማመልከቻ ከቀረበለት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር በስልሳ(60) ተከታታይ የካላንደር ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ ፈቃድ የሚሰጠው መሆን አለመሆኑን ባለሥልጣኑ ለአመልካቹ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት።

8. **ፈቃድ ስለመከልከል**

1/ አመልካቹ የሚከተሉትን አለማሟላቱን ባለሥልጣኑ ሲያረጋግጥ ለአመልካቹ ፈቃድ ሊከለክል ይችላል፡-

ሀ) የዚህን መመሪያ መስፈርቶች ሳያሟላ የቀረ እንደሆነ፤

ለ) በተገቢው አቅም ስራውን እና ተግባራትን ለማከናወን የሚያስችል ብቃት ያለው የሰው ኃይል ያለው መሆኑን ያላሳየ እንደሆነ፤

ሐ) ሃሰተኛ ወይም አሳሳች መረጃ ያቀረበ እንደሆነ፤

መ) የፈቃድ ማመልከቻ በሚቀርብበት ጊዜ ለባለሥልጣኑ መቅረብ የነበረበትን መሠረታዊ ፍሬ ነገረ ወይም መረጃ ሳያቀርብ የቀረ እንደሆነ፤ወይም

ሠ) ከአዋጁ፣ ወይም ከባለሥልጣኑ መመሪያዎች ጋር የማይጣጣም ውስጠ-ደንብ ወይም ፖሊሲ ያለው ከሆነ፤ ወይም የአዋጁን፣ ተያያዥ ደንቦችን እና የመመሪያዎቹን ማንኛውም ድንጋጌዎች የጣሰ እንደሆነ።

2/ እያንዳንዱ አመልካች ያቀረበው ማመልከቻ ውድቅ ከመደረጉ ወይም ፈቃድ ከመከልከሉ በፊት በባለሥልጣኑ የመሰማት እድል ሊሰጠው ይገባል፡፡

## 9. **ፈቃድ ስለማደስ፣ ስለማገድ እና ስለመሰረዝ**

1/ የአዋጁ አንቀጽ 33 ንዑስ አንቀጽ (3)-(10) እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ በአዋጁና በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱት መመዘኛዎችና መስፈርቶች የተሟሉ መሆናቸውን በመገምገም በዚህ መመሪያ መሠረት የሰጠውን ፈቃድ ሊያድስ፣ ሊያግድ ወይም ሊሰርዝ ይችላል፡፡

2/ በዚህ መመሪያ መሰረት የተሰጠ ፈቃድ በየአመቱ መታደስ ያለበት ሲሆን ለባለስልጣኑ የሚቀርብ የእድሳት ማመልከቻ የነባሩ ፈቃድ ጊዜ ከማብቃቱ ከአንድ (1) ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡

3/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ላይ በተገለጸው መሠረት አመልካች በባለሥልጣኑ የመሰማት ዕድል ሳይሰጠው ባለሥልጣኑ የእድሳት ማመልከቻን ውድቅ ማድረግ የለበትም፡፡

## 10. **ስለክፍያዎች**

እያንዳንዱ አመልካች በባለሥልጣኑ የክፍያ መመሪያ በተገለጸው መሠረት ክፍያዎችን መፈጸም አለበት፡፡

## ክፍል ሁለት

## የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ

### 11. ገበያውን ራሱን በራሱ ለሚቆጣጠር ድርጅት የሚያበቁ መስፈርቶች

1/ የገበያ ፈቃድ አመልካች፦

ሀ) ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት መስፈርቶችን ማሟላት፤ እና

ለ) በአዋጁ ክፍል ሶስት እና በዚሁ መሠረት በወጡ መመሪያዎች መሰረት ራሱን በራሱ እንደሚቆጣጠር ድርጅት ስራውን መወጣት እንደሚችል ማሳየት፤

አለበት።

2/ አመልካቹ በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ሲያሟላ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ወይም የተዛማጅ ውሎች ገበያ ለማቋቋም ወይም ለማከናወን ዓላማ የገበያ ፈቃድ ይሰጠዋል።

3/ የገበያ ፈቃድ ሲሰጥ እና በአዋጁ አንቀጽ 23 መሠረት፦

ሀ) ባለሥልጣኑ ለገበያው የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት እንዲሁም ማናቸውንም ሁኔታዎች በጽሑፍ መግለጽ፤ እና

ለ) ገበያው እሱን ወክሎ እንዲሠራ ስልጣን ስለሰጠው ሰው በጽሑፍ ማሳወቅ፤

አለበት።

### 12. ስለገበያ ፈቃድ መስፈርቶች

1/ የገበያ ፈቃድ ማመልከቻ በዚህ መመሪያ ክፍል ሁለት ውስጥ የተቀመጡትን መስፈርቶች መሟላቱን ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች ሁሉ ማካተት አለበት።

2/ አመልካቹ የሚከተሉት ያሉት መሆኑን ማሳየት አለበት፦

ሀ) በዚህ መመሪያ ውስጥ የተገለጹት ዝቅተኛ የካፒታል መስፈርቶች፤

ለ) ገበያው በባለቤትነት እና በቁጥጥር፣ በአስተዳደር እና በአመራር አደረጃጀቶች በአግባቡ የተደራጀ መሆኑን፤

ሐ) በቂ እና ተገቢ የሰው ኃይል እንዲሁም የቴክኖሎጂ ክህሎት፤

መ) ተገቢ የሆነ የግብይት መሰረተ-ልማት፣ ቴክኖሎጂ እና ሥርዓቶች፤

ሠ) በቂ እና ውጤታማ የአሰራር ፖሊሲዎች እና ሥነ-ሥርዓቶች፤

ረ) ለአባላቱ እና ለሚያከናውናቸው ተግባራት ተገቢው ውስጠ-ደንብ፤

ሰ) ለሰነደ ሙዓለ ንዋይ ምዝገባ እና ግብይት ተገቢው ዝግጅት፤

ሸ) በሚያከናውነው የግብይት መድረክ ላይ በቂ ቁጥጥር፣ ቅኝት እና ክትትል ማድረግ የሚችል መሆኑን፤

ቀ) ከባለሥልጣኑ ስልጣን ከተሰጠው ማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት ወይም ፈቃድ ከተሰጠው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ጋር አስፈላጊው ትስስር የፈጠረ መሆኑን፤

በ) ከአደጋ ተመልሶ የማገገም ዝግጅቶችን ያካተተ የተሰነደ ሥራን የማስቀጠል እቅድ፤እና

ተ) ከሥራው፣ ከትግበራው እና አሰራር፣ ከቴክኖሎጂው እና ከቁጥጥር ህግ-አክባሪነት ጋር በተገናኘ ተገቢው የአደጋ አስተዳደር ዝግጅቶች።

## 13. ስለዝቅተኛ የካፒታል መስፈርቶች

1/ ለገበያ ፈቃድ ዝቅተኛው የተከፈለ ካፒታል ብር 500,000,000.00 (አምስት መቶ ሚሊዮን ብር) ነው።

2/ ባለሥልጣኑ ዝቅተኛውን የካፒታል መስፈርቶች እንደ ገበያው የሥራ እና የክወና ተፈጥሮ እና መጠን እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅ ስጋቶችን መሠረት በማድረግ በየጊዜው ማስተካከል ይችላል።

3/ ማንኛውም የታቀደ የዝቅተኛ ካፒታል መጠን ማሻሻያ ገበያው እንዲያሟላ በቂ ጊዜ የሚሰጥ ሆኖ ባለሥልጣኑ በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል።

4/ በመመስረቻ ጽሁፉ እና እንደአገባቡ በንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀቱ ላይ የተመለከተው የካፒታል መጠን በዚህ አንቀጽ መሰረት ከሚፈለገው ዝቅተኛ የተከፈለ ካፒታል ጋር እኩል ወይም የሚበልጥ መሆን አለበት።

5/ ገበያው የሚከተሉትን ለማከናወን የሚያስችሉት በቂ የጥሬ ገንዘብ እና ገንዘብ-አከል ሀብት የሚያካትት ካፒታል ሊኖረው ይገባል፦

ሀ) ማንኛውንም የካፒታል ወጪ እና የስራ ማካሄጃ ወጪን ጨምሮ አሁን እያከናወነ ያለውን እና ያቀዳቸውን ሥራዎችና ክንውኖች ለማስቀጠል የሚያስችል፤

ለ) የተገመገሙትን የስጋት ሁኔታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት ቢያንስ የአንድ አመት የወደፊት ጊዜን ለመሸፈን፤ እና

ሐ) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ገበያውን በአግባቡ ለመቀነስ ወይም ለመዝጋት የሚያስችል።

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) የተገለጸው ቢኖርም የገበያው ጥሬ ገንዘብ እና ገንዘብ-አከል ሀብት የጠቅላላ ሀብቱን ቢያንስ ሃያ በመቶ (20%) መሆን አለበት።

7/ ገበያው በማንኛውም ጊዜ የዚህን አንቀፅ መስፈርቶች አሟልቶ መገኘት ያለበት ሲሆን ለገበያው ፈቃድ በሚያመለክትበት ጊዜም ሆነ በቀጣይነት ለባለሥልጣኑ ሪፖርት ለማቅረብ ባለበት ግዴታ መሠረት የዚህን

አንቀፅ መስፈርቶች የሚያሟላ ስለመሆኑ የፋይናንስ ስጋት ምርመራ እና የፋይናንስ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

**14. <u>የገበያ ፈቃድ</u>**

በዚህ መመሪያ መሰረት የተገኘ የገበያ ፈቃድ የሚከተሉትን ያካተተ መሆን አለበት፡-

1/ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ፣ የተዛማጅ ውሎች ገበያ ወይም ሁለቱንም የሚመለከት መሆኑን፤

2/ ለግብይት የተፈቀዱ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ዓይነቶች እና በሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ ለመገበያየት የተፈቀደላቸው የሚመለከታቸው ኢንቨስተሮች ክፍልን ጨምሮ በፈቃዶቹ ለመስራት የተፈቀዱ ተግባራት እና አገልግሎቶችን፤ እና

3/ በባለሥልጣኑ የተጣሉ ማናቸውም ገደቦች ወይም ልዩ ሁኔታዎች፡፡

**15. <u>በገበያው ላይ ስለተጣሉ ገደቦች</u>**

ገበያው በድርሻ የተያዘ ወይም በገቢ የተገኘ የራሱን ካፒታል በመጠቀም የግብይት ትዕዛዞችን ማስፈጸም እና በማንኛውም በሚያዝበት የግብይት መድረክ፣ ገበያ ወይም አገልግሎት ለራሱ ማንኛውንም ግብይቶችን መፈጸም የለበትም፡፡

**16. <u>ስለገበያው አደረጃጀት</u>**

1/ ገበያው በማንኛውም ጊዜ ተገቢው ባለቤትነት፣ ቁጥጥር፣ አመራር እና አስተዳደር ያለው መሆኑን፣ እና ብቃቱን እና ታማኝነቱን፤ በማስረጃ ማረጋገጥ አለበት፡፡

2/ ገበያው በባለአክስዮንነት ወይም በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ጉልህ ተፅዕኖ ሊፈጥርበት ከሚችል የተፈጥሮ ወይም ሕጋዊ ሰው ጋር የቅርብ ግንኙነት ካለው፣ ይህ ግንኙነት ባለሥልጣኑ የሚያደረገውን ውጤታማ ቁጥጥር የማያደናቅፍ እና የገበያውን የስራ ክንውን፣ የሕግ አክባሪነት እና የአዋጁና የዚህ መመሪያ መስፈርቶችን አክብሮ መስራት ላይ ችግር የማይፈጥር መሆኑን ገበያው በተገቢ ሁኔታ ለባለሥልጣኑ ማሳየት ይኖርበታል፡፡

3/ ገበያው ድርጅታዊ መዋቅሩ እና ስለባለቤቶቹ፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተገለጸው በተለይ የቅርብ ግንኙነት ያለውን ወገን ማንነት እና ያለውን ጥቅም እና ቀጣይነት ያላቸውን ለውጦችን በተመለከተ ለባለሥልጣኑ መረጃ መስጠት እንዲሁም ለሕዝብ ማሳወቅ አለበት፡፡

4/ ገበያው ባለሥልጣኑ የሚያወጣውን የድርጅት አመራር ማስታወቂያ፣ አቅጣጫ፣ ወይም መመሪያ መተግበር አለበት፡፡

**17. <u>ስለዳይሬክተሮች ቦርድ</u>**

1/ ባለሥልጣኑ በሚከተሉት ምክንያቶች ለዳይሬክተሮች ቦርድ እጩ አባል ይሁንታውን ላይሰጥ ይችላል፡-

ሀ) እጩ አባሉ መልካም ስም፣ ገበያውን ለመምራት የሚያስችል ተገቢው እውቀት እና ክህሎት፣

ተዛማጅ ልምድ እና ሥራውን ለማከናወን የሚያስችል በቂ ጊዜ የሌለው ከሆነ፤ ወይም

ለ) የቀረበው እጩ አባል የገበያውን ውጤታማ እና ጥንቃቄ የተሞላበት አስተዳደርን ወይም የገበያውን

ታማኝነት አደጋ ላይ እንደሚጥል ተጨባጭ እና ተገቢ ምክንያቶች ካሉ፡፡

2/ እያንዳንዱ የቦርድ አባል በአባልነት ባለበት ጊዜ ሁሉ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማሟላት አለበት፡-

ሀ) ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶች እውቅና ለመስጠት በባለሥልጣኑ በወጣው መመሪያ መሠረት የተቀመጡትን የብቁነት እና ተገቢነት መሥፈርቶች፤

ለ) ግዴታዎቹን ለመወጣት የሚያስችለው በቂ እውቀት፣ ክህሎት እና ልምድ ያለው፤

ሐ) ሥራውን ለማከናወን የሚያስችል በቂ ጊዜ የሚሰጥ፤እና

መ) አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሁሉ የከፍተኛ አመራሩን ውሳኔ አሰጣጥ እና የቁጥጥር ሥራ በተሳካ ሁኔታ ለመቆጣጠር፣ በአግባቡ ለመመርመር እና ለመገዳደር በታማኝነት፣ በሃቀኛነት እና በገለልተኛነት መስራት የሚችል፡፡

**18. <u>ስለአስተዳደር መዋቅር</u>**

1/ ገበያው አዋጁን፣ ተዛማጅ ደንቦችንና መመሪያዎችን በማክበር እንደሚሰራ ለማረጋገጥ፡-

ሀ) በገበያው ተገቢው የስራ ኃላፊነት ክፍፍል፣ ውጤታማ የውሳኔ አሰጣጥ መዋቅሮች እና የጥቅም ግጭት እንዳይከሰት መከላከልን ጨምሮ ውጤታማ እና በጥንቃቄ የተሞላ የአስተዳደር መዋቅር ያለው መሆን፤ እና

ለ) የገበያውን አስተዳደር የውሳኔ አሰጣጥ መከታተልና የገበያውን አሠራር ተገቢውን ቁጥጥር ማድረግን ጨምሮ የዳይሬክተሮች ቦርድ በአዋጁና በመመሪያው የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት መረጃዎችን እና ሰነዶችን ማግኘቱን ማረጋገጥ፤

አለበት፡፡

2/ የዳይሬክተሮች ቦርድ በየጊዜው የአስተዳደር መዋቅሮችን ውጤታማነት በመገምገም ጉድለቶችን ለመፍታት ተገቢውን እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡

**19. <u>ስለዋና ስራ አሥፈፃሚ</u>**

ባለሥልጣኑ የዋና ሥራ አስፈፃሚውን ሹመት በሚከተሉት ምክንያቶች ይሁንታ ሳይሰጥ ይችላል፡-

1/ ተሿሚው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያን ለመምራት ተገቢው ሙያ፣ እውቀት፣ ክህሎት እና ልምድ የሌለው ከሆነ፤ወይም

2/ ተሿሚው ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶች እውቅና ለመስጠት በባለሥልጣኑ በወጣው መመሪያ መሠረት የተቀመጡትን የብቁነት እና ተገቢነት መሥፈርቶች የማያሟላ ከሆነ፡፡

## 20. ስለገበያው ከፍተኛ ባለሙያዎች

1/ የገበያው ከፍተኛ ባለሙያዎች በአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (71) በተሰጠው ትርጉም መሠረት የኦፕሬሽን ከፍተኛ መኮንን፣ የፋይናንስ ከፍተኛ መኮንን፣ የስጋት እና ህግ ማስከበር ከፍተኛ መኮንን እና በባለሥልጣኑ እንዳስፈላጊነቱ ማናቸውም ከፍተኛ ደረጃ ባለሙያ ተብለው የተለዩትን ያካትታል።

2/ ገበያው የሚጠቀምበት የሥራ መደብ ወይም ስያሜ ቢኖርም የገበያውን ቴክኖሎጂ ነክ ጉዳዮችን የመቆጣጠርና የማስተዳደር እንዲሁም የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ እና ከምዝገባ ስረዛ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ኃላፊነት ያለባቸው ባለሙያዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ከፍተኛ ባለሙያ ተብለው መለየት አለባቸው።

3/ የገበያው ከፍተኛ ባለሙያ ተብሎ የተለየ ባለሙያ፡-

ሀ) ተገቢው ሙያዊ ብቃት፣ እውቀት፣ ክህሎት እና ልምድ ያለው፤ እና

ለ) ራሳቸውን በራሳቸው ለሚቆጣጠሩ ድርጅቶች እውቅና ለመስጠት ባለሥልጣኑ ባወጣው መመሪያ መሠረት የተቀመጡትን "የብቁ እና ተገቢነት" መሥፈርቶች የሚያሟላ፤

መሆን አለበት።

4/ ገበያው ከፍተኛ ባለሙያዎቹ ራሱን በራሱ ከሚቆጣጠር ድርጅት ከፍተኛ ባለሙያዎች የሚፈልገውን ፈተና በተሳካ ሁኔታ ማለፋቸውን ለባለሥልጣኑ ማስረጃ ማቅረብ አለበት።

## 21. የሰው ኃይል እና የቴክኒክ ክህሎት

1/ ገበያው ስራውን ለማከናወን እንዲያስችለው አስፈላጊው ክህሎት እና በቂ እውቀት ያላቸው የሰራተኛ መጠን መቅጠር፤ እና ሰራተኞቹ ከጊዜው ጋር የተጣጣመ ክህሎት ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ እና ክህሎታቸውን በየጊዜው መመዘን አለበት።

2/ የገበያው የሰው ሀብት መስፈርቶች የሥራውን ባሕሪ፣ ደረጃ እና የስራውን ውስብስብነት ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን ሲኖርበት ገበያውም የሰው ሀብት መስፈርቶቹን በየጊዜው መገምገም አለበት።

3/ ገበያው ሁልጊዜ የሚከተሉት ሠራተኞች ሊኖሩት ይገባል፡-

ሀ) ራሱን በራሱ እንደሚቆጣጠር ድርጅት በውክልና በተሰጠው ተግባር መሠረት አግባብነት ያላቸው የቁጥጥር ሠራተኞች፤

ለ) ተገቢ የስጋት እና ህግ ማስከበር ሠራተኞች፤እና

ሐ) የውስጥ ኦዲት ሠራተኞች።

4/ ከፍተኛ የስጋት እና የህግ ማስከበር ባለሙያ እና ከፍተኛ የውስጥ ኦዲት ባለሙያ የሚሾሙት በገበያው የዳይሬክተሮች ቦርድ ሲሆን በቀጥታ ሪፖርት የሚያደርጉትም ለቦርዱ ይሆናል።

## 22. ስለስጋት እና ሕግ ማስከበር

1/ ገበያው ተያያዥ ስጋቶችን በአጠቃላይ ለማስተዳደር እና ለመቆጣጠር የሚያስችል ተገቢ የሆነ የስጋት አስተዳደር ማዕቀፍ ሊኖረው ይገባል።

2/ በገበያው የተተገበረው የስጋት አስተዳደር ዝግጅት በቂነት እና ውጤታማነት በዚህ መመሪያ ተለይተው በተቀመጡ መስፈርቶች ማዕቀፍ እና በዚህ መመሪያ ውስጥ በተመለከቱት በገበያው ቀጣይ ግዴታዎች እና የቁጥጥር ዝግጅቶች አካል ይገመገማል፡፡

3/ ገበያውን በገለልተኝነት የመቆጣጠር ኃላፊነት ያለበት የስጋት እና የህግ ማስከበር ክፍል ገበያው ሊኖረው ይገባል፡፡

4/ የስጋት እና የሕግ ማስከበር ክፍል ኃላፊነት የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

ሀ) ገበያው በአዋጁ እና በመመሪያዎች የተቀመጡ መስፈርቶችን እና ግዴታዎችን እየተገበረ እና እያከበረ መሆኑን ቁጥጥር ማድረግ፤ እና

ለ) ገበያው በዚህ አንቀጽ የተቀመጡ መስፈርቶች እና ግዴታዎች እንዲያከብር ለማስቻል ፖሊሲዎችን እና ሥነ-ሥርዓቶች ማዘጋጀት እና መያዝ፡፡

5/ የስጋት እና የሕግ ማስከበር ክፍል ሠራተኞች ቢያንስ የሚከተሉትን ጉዳዮች በተመለከተ አጠቃላይ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል፡-

ሀ) በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ ስለተመለከቱ የሕግ እና የቁጥጥር ግዴታዎች፤

ለ) ግብይቱ፣ የግብይት ሥርዓቱ እና የግብይት ስልተ-ቀመሮች እንዴት እንደሚሰሩ፤

ሐ) ስለገበያው የግብይት መድረክ እና ሥርዓት ተገቢው እውቀት፤ እና

መ) በገበያው እየተከናወኑ ስላሉ የግብይት ዓይነቶች፡፡

6/ የሚመለከተው የስጋት እና የሕግ ማስከበር ከፍተኛ ባለሙያ የስጋት እና የሕግ ማስከበር ሪፖርትን በገበያው መቅረብ ያለባቸው የሪፖርት ግዴታዎች አካል አድርጎ እና በባለሥልጣኑ በተጠየቀ ጊዜ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

7/ ለገበያው የስጋት እና የሕግ ማስከበር ክፍል የሚመደበው የሰው ኃይል እና የቴክኒክ ሀብት ገበያው ለሚሰራው ሥራ መጠን እና ውስብስብነት ተገቢ መሆን አለበት፡፡

8/ ገበያው በሚያካሄደው የሥራ መጠን እና ውስብስብነት ላይ ተመስርቶ በአደረጃጀቱ ውስጥ ለስጋት እና ለሕግ ማስከበር ስራዎች ሁለት የተለያዩ የስጋት እና የሕግ ማስከበር ክፍሎች እንደሚያስፈልገው ባለሥልጣኑ ካመነበት ሁለት ክፍሎች እንዲያቋቁም ሊያዝ ይችላል፡፡

## 23. ሥራን በሦስተኛ ወገን ስለማሰራት

1/ ገበያው የሚከተሉት ሁኔታዎችን ሲያሟላ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ሥራዎችን በሦስተኛ ወገን አገልግሎት ሰጪ ሊያሰራ ይችላል፡-

ሀ) ገበያው ለባለሥልጣኑ ያለበትን ኃላፊነት የማይገድብ ከሆነ፣

ለ) የገበያው ከፍተኛ አመራር አባላትን ኃላፊነት ለሌላ አሳልፎ የማይሰጥ ከሆነ፣

ሐ) የገበያ ቁጥጥር እና የግብይት ክትትል ሥራ ውጤታማነት ላይ በማናቸውም መልኩ እንቅፋት ሊፈጥርበት የማይችል ከሆነ፤እና

መ) ገበያው ከአባላቱ፣ ከአውጪዎች ወይም ኢንቨስተሮች ጋር ያለውን ግንኙነት ወይም ግዴታዎች የማይለውጥበት ከሆነ።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተደነገገው ቢኖርም የሚከተሉትን ስራዎች አፈጻጸም በሦስተኛ ወገን እንዲሰራ ሊሰጥ አይችልም፡-

ሀ) በግብይት ስርዓት ላይ ያለን የግብይት ክትትል እና የገበያ ቁጥጥር ሥራ፤

ለ) የገበያው አባላትን የመቀበል፣ የማስወጣት እና የማገድ ሥራ፤

ሐ) የግብይት ሥርዓቱን በመጠቀም ከተለመደው ውጪ፣ የተለዩ ወይም ጊዜያዊ መልዕክት የመቀበል ሥራ፤

መ) ግብይት የማስቆም ወይም የማገድ ሥራ ላይ የሚሰጥ ውሳኔ፤ወይም

ሠ) የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ለግብይት ምዝገባ ወይም ቅበላ ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ከምዝገባ የመሰረዝ ወይም ከግብይት የመሰረዝ ውሳኔ።

3/ የሦስተኛ ወገን አገልግሎት ሰጪው ተገቢው የክህሎት ስብስብ ሊኖረው እና የተሰጠውን ተግባር ማከናወን መቻል አለበት።

4/ ገበያው ሥራውን በሦስተኛ ወገን አገልግሎት ሰጪ በማሰራቱ ለአላስፈላጊ ወይም ተቀባይነት ለሌለው ስጋት የማያጋልጥው መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

5/ በገበያው እና በሦስተኛ ወገን አገልግሎት ሰጪ መካከል የሚደረገው ስምምነት መብት እና ግዴታዎችን በግልጽ አካቶ በጽሁፍ መቀመጥ ይኖርበታል።

6/ ገበያው ከሦስተኛ ወገን አገልግሎት ሰጪ ስራውን ለመስጠት ከመስማማቱ በፊት፡-

ሀ) ሥራን በውጭ አካል የማሰራት ፍላጎቱን ለባለሥልጣኑ በጽሁፍ ማሳወቅ፤

ለ) የሦስተኛ ወገን ስምምነቱ የዚህ አንቀጽ መስፈርቶች ስለመሟላቱ ያለውን ግምገማ ማቅረብ፤ እና

ሐ) ከባለሥልጣኑ ተቃውሞ የሌለ ስለመሆኑ የጽሁፍ ማረጋገጫ ማግኘት፤

አለበት፡፡

## 24. የግብይት መድረኮች ወይም ሥርዓቶች ጠቅላላ መስፈርቶች

1/ የገበያው የግብይት መድረክ ወይም ሥርዓት የሚከተሉት ውጤታማ ሥርዓቶች፣ የአሰራር ሥነ-ሥርዓቶች እና ዝግጅቶች ሊኖሩት ይገባል፦

ሀ) ጫናን የሚቋቋም፤

ለ) ከፍተኛ መጠን ያላቸው ትዕዛዞችና መልዕክቶች ለመቀበል የሚያስችል በቂ አቅም፤

ሐ) ከፍተኛ የገበያ ጫና በሚኖርበት ሁኔታ ግብይት በሥርዓቱ ለማካሄድ የሚያስችል፤ እና

መ) አስቀድሞ ከተወሰነ መጠን እና የዋጋ ገደብ በላይ ወይም ግልጽ ስህተት ያለበትን ትዕዛዝ ውድቅ ማድረግ የሚችል፡፡

2/ ገበያው የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መስፈርቶች፦

ሀ) ቅድመ-ሁኔታዎቹ ስለመሟላታቸው ለማረጋገጥ ሙሉ ፍተሻ የተደረገላቸው መሆኑን፤ እና

ለ) የግብይት ሥርዓቱ እክል በሚገጥምበት ጊዜ አገልግሎት መስጠት መቀጠል የሚያስችል ውጤታማ የሆነ የንግድ ቀጣይነት ዝግጅት ያላቸው እና ስርዓት የተዘረጋላቸው መሆኑን፤

ማረጋገጥ አለበት፡፡

## 25. የግብይት መድረክ ወይም ሥርዓት ብቃት

1/ ገበያው የግብይት መድረኩ ወይም ሥርዓቱ ግብይቶችን በማዛመድ ሂደት ወቅት መበላሸት፣ መቋረጥ ወይም ስህተት ሳይኖር ስራውን ለማከናወን የሚያስችል በቂ አቅም እንዳለው ማረጋገጥ አለበት፡፡

2/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ለተጠቀሰው አላማ የግብይት ሥርዓቱ አላባዎች የሚከተሉትን ተግባራት የሚደግፉ መሆን አለባቸው፦

ሀ) ትዕዛዝ ማስገቢያን ጨምሮ ከተገልጋይ ወደ መረጃ ቋት የመረጃ ፍሰት መስመር ግንኙነት፣ ትዕዛዝ የማስገባት አቅም፣ የትዕዛዝ አገባብ መቆጣጠሪያ አቅም እና በተለያዩ በትዕዛዝ መግቢያዎች የደንበኞች ትዕዛዞችን አመጣጥኖ መቀበል እንዲችል፤

ለ) የግብይት ትዕዛዞች የሚተላለፉበትን ጨምሮ የግብይት ስርዓቱን በበቂ መዘግየት ትዕዛዞችን የማዛመድ ችሎታ፤

ሐ) ግብይት መፈጸምን ጨምሮ ከመረጃ ቋት ወደ ተገልጋይ የመረጃ ፍሰት መስመር ግንኙነት፣ ትዕዛዝ እና የግብይት ማስተካከያ እና ማንኛውም ሌላ አይነት የግብይት መረጃ ግብዓት እንዲሆን፤እና

መ) በዚህ አንቀጽ የተጠቀሱት አላባዎች አፈፃፀም ለመቆጣጠር የሚያስችል መሠረተ ልማት፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ለተጠቀሰው አላማ በቂ አቅም የሚለካው የሚከተሉትን ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡-

ሀ) ትዕዛዞችን እና ማስተካከያዎችን፣ ወይም ትዕዛዝ መሠረዝን ጨምሮ ማንኛውም ወደ ግብይት ሥርዓቱ የሚገባ ግብዓት፤ እና

ለ) ወደ ግብይት ሥርዓቱ ለሚገባ ግብዓት የግብይት ሥርዓቱ የሚሰጠውን ምላሽ፣ የትዕዛዝ መዝገብ መረጃ ማሳየት፣ የግብይት ሥርዓቱን አቅም በመጠቀም ከግብይት በኋላ የሚመጣን መረጃ ማሰራጨትን፡፡

4/ ገበያው የሚከተሉትን ማረጋገጥ አለበት፡-

ሀ) የግብይት ሥርዓቱ መልዕክቶች በፍጥነት በሚጨምሩበት ጊዜ የሥርዓቱ ብቃት ጉልህ በሆነ መልኩ ሳይቀንስ መቋቋም የሚችል መሆኑን፤ እና

ለ) የግብይት ሥርዓቱ ንድፍ አስፈላጊ በሆነበት ወቅት እና ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ አቅሙን ለማስፋፋት በሚያስችል መልኩ የተሰራ መሆኑን፡፡

5/ ገበያው የግብይት ሥርዓቱ ተገቢውን የመልዕክት መጠን ለመመዝገብ የሚያስችል ስለመሆኑ በአመት አንድ ጊዜ መገምገም ያለበት ሲሆን ከግምገማው በኋላ ገበያው አቅሙን ለማሳደግ ሊወስድ ያቀደውን ማናቸውንም እርምጃዎች እና ይህንኑ የሚተገበርበትን ጊዜ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

6/ ገበያው ማንኛውንም መሠረታዊ የግንኙነት መቋራረጥ ጨምሮ ከባድ የግብይት መቋረጥ ሲያጋጥመው ወዲያውኑ ለሕዝብ ይፋ ማድረግና ለባለሥልጣኑ እና ለአባላቱ ማሳወቅ አለበት፡፡

**26. <u>ስለግብይት መድረኮች ወይም ሥርዓቶች አቅም</u>**

1/ የአዋጁ አንቀጽ 33 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) እንደተጠበቀ ሆኖ በገበያው በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በአጭር ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ መጠን ያለው የዋጋ ለውጥ የተከሰተ እንደሆነ ገበያው በጊዜያዊነት ግብይት ማቆም ወይም መገደብ ያለበት ሆኖ በልዩ ሁኔታ ማንኛውንም ግብይት መሰረዝ፣ መለወጥ ወይም ማስተካከል አለበት፡፡

2/ ገበያው ሥርዓቱን ያልተከተለ የግብይት ሁኔታን ለማስተካከል፤ የሚከተሉትን ማድረግ የሚያስችል ውጤታማ ሥርዓት፣ የአሰራር ሥነ-ስርዓት እና ዝግጅት ሊኖረው ይገባል፡-

ሀ) የግብይት ሥርዓቱ የመጨረሻ አቅም ሲጠቀም እና የማስተናገድ አቅም ስጋት ሲኖር ወደ ሥርዓቱ የሚገቡ ትዕዛዞችን ፍሰት ማዘግየት፤

ለ) በግብይት ሥርዓቱ ተፈፃሚ የሚሆነውን ዝቅተኛ የዋጋ እንቅስቃሴ መጠን መገደብ እና ተግባራዊ ማድረግ፤

ሐ) አባላት ወይም ድጋፍ ያለው ተሳትፎ ተጠቃሚዎች የግብይት ሥርዓቱን ስልተ-ቀመር በትክክል እንደሚሰራ መፈተሽን ወይም ፍተሻ እንዲካሄድ ምቹ ሁኔታን መፍጠርን ጨምሮ የግብይት ሥርዓቱ ስልተ-ቀመሮች ሥርዓትን ያልተከተለ የግብይት ሁኔታ እንደማይፈጥሩ ወይም ተጽእኖ እንደማያደርጉ ማረጋገጥ፤ እና

መ) ወደ ግብይት ሥርዓቱ የገቡ የማይፈጸሙ ትዕዛዞች ምጣኔ መገደብን ጨምሮ ከግብይት ስልተ-ቀመር የሚመነጭ ማናቸውም ሥርዓት ያልተከተለ የግብይት ሁኔታን ለማስተዳደር የሚያስችል፡፡

3/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) አላማ ገበያው፦

ሀ) የግብይት ማስቆሚያ መመዘኛዎች የተለያዩ የሀብት ክፍሎችን እና የንዑስ ክፍሎች ሁሌም የመሸጥና የመግዛት እድል በበቂ ሁኔታ መኖሩን፣ የግብይት ሞዴል ባህሪ፣የተጠቃሚዎቹን አይነት ከግምት ውስጥ ያስገባ እና ግብይቱ ሥርዓቱን በጠበቀ መልኩ ጉልህ መስተጓጉሎችን ለማስወገድ በቂ የሆነ እና በአግባቡ ፍተሻ የተደረገለት መሆኑን ማረጋገጥ፤

ለ) የግብይት ማስቆሚያ መመዘኛዎች እና በነዚህ መመዘኛዎች ላይ የሚያደርገውን መሠረታዊ ለውጥ በቀጣይነት እና ተነፃፃሪ በሆነ ሁኔታ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ፤እና

ሐ) ግብይትን በተጨባጭ ለማስቆም ወይም ለመገደብ ወይም ግብይትን ለማቆም መመዘኛዎችን ለማቋቋም ወይም ለማሻሻል የባለሥልጣኑን የጽሑፍ ፈቃድ ማግኘት፤

አለበት፡፡

4/ ገበያው በስልተ-ቀመሩ የሚፈጠሩ ትዕዛዞችን፣ ትዕዛዝ ለመፍጠር የሚውሉ የተለያዩ ቀመሮችን እና እነዚህን ትዕዛዞች የሚያወጡ ሰዎችን መለየት እና በሚጠየቅበት ጊዜም ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

## 27. <u>የግብይት መድረክ ወይም ሥርዓት ለመጠቀም የሚቻልበት ሁኔታዎች</u>

1/ ገበያው አባላቱ የኤሌክትሮኒክ ትዕዛዝ ማስገቢያ ሥርዓት ስለሚጠቀሙበት ቅድመ- ሁኔታዎች አሰራር ያወጣል፡፡

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቋቋሙ ቅድመ ሁኔታዎች በግብይት መድረኩ ወይም ሥርዓቱ የሚከናወኑ የግብይት አይነቶችን ከግምት ውስጥ ያስገቡ ሆነው ቢያንስ የሚከተሉትን ማካተት አለባቸው፡-

ሀ) በአባላቱ የግብይት እንቅስቃሴ ላይ የቅድመ-ግብይት ዋጋ ቁጥጥር፣ የትዕዛዞችን መጠን እና ዋጋ፣ የሥርዓቱ አጠቃቀም እና የድህረ-ግብይት ቁጥጥር፤

ለ) የግብይት መድረኩን ወይም ስርዓቱን በሚጠቀሙ ወይም በሚሳተፉ አባላት ውስጥ ያሉ ሰራተኞች ተፈላጊ ብቃት፤

ሐ) በአባላት የሚከወን የቴክኒክ እና የአፈፃፀም ተስማሚነት ፍተሻ፤

መ) ሥርዓት-ያልተከተለ የግብይት ሁኔታዎችን ለመከላከል ሲባል ያልተፈጸሙ ግብይቶችን ለመሰረዝ የማቋረጥ ተግባርን የመጠቀም ፖሊሲ፤እና

ሠ) አባሉ ለደንበኞቹ በቀጥታ በኤልክትሮኒክ መሳርያ የመሳተፍ መብት የሚሰጣቸው መሆን አለመሆኑን የሚገልፅ ድንጋጌ እና የሚሰጣቸው ከሆነ ለነዚህ ደንበኞች ተፈፃሚ የሚሆነውን ቅድመ ሁኔታ፡፡

3/ ገበያው፡-

ሀ) ባለሥልጣኑ ግብይት መቆጣጠር እንዲችል ከትዕዛዝ መመዝገቢያ መዝገብ ጋር የተያያዘ ዳታ ማቅረብ ወይም ባለሥልጣኑ የትዕዛዝ መዝገቡን ማየት እንዲችል ማድረግ፤ እና

ለ) ባለሥልጣኑ አስፈላጊውን ማጣራት ወይም ምርመራ እንዲያደርግ የድህረ-ግብይት መረጃ የተመዘገበበትን ተገቢ መዝገብ መያዝ እና ማቅረብ፤

አለበት፡፡

## 28. ሥርዓት፣ ቁጥጥር እና የአስተዳደር መዋቅር

1/ ገበያው በሚከተሉት በበቂ ሁኔታ የተደራጀ መሆን አለበት፡-

ሀ) ለሥራው ዋና ሥጋቶችን ለመለየት የሚያስችለው ተገቢ የሆነ መዋቅር እና ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ፤ እና

ለ) ተጋላጭ የሆነባቸውን ስጋቶች በውጤታማነት ለመቀነስ እና ለማስተዳደር፡፡

2/ ገበያው፡-

ሀ) ሊከሰት የሚችልን የሥርዓት መቆራረጥ በተገቢ ለማስተዳደር የሚያስችል ውጤታማ መጠባበቂያ እቅድ ማዘጋጀትን ጨምሮ የቴክኒክ ስራው የሚመራበትን ጠንካራ የአስተዳደር ሥርዓት መተግበር፤እና

ለ) በሥርዓቱ ላይ የሚከናወኑ ግብይቶችን በስኬት እና በጊዜው እንዲጠናቀቁ የሚያስችል ውጤታማ መዋቅር ያለው መሆን፤

አለበት፡፡

3/ ገበያው የሚከተሉትን በግልጽ ለመለየት እና ለማስተዳደር የሚያስችል መዋቅር ሊኖረው ይገባል፦

ሀ) የግብይት መድረኩ ወይም ሥርዓቱ ክዋኔ ሊያስከትል የሚችለውን ማንኛውንም አሉታዊ ውጤት፤ እና

ለ) የግብይት መድረኩን ወይም ስርዓቱን ወይም በባለሥልጣኑ የተሰጡትን ማንኛውንም ተግባራት፣ ግዴታዎች እና ኃላፊነቶች ለመወጣት ባለው አቅም ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል ማንኛውም የጥቅም ግጭት፡፡

## 29. ሥርዓት ያልተከተሉ የግብይት ሁኔታዎችን ስለመከላከል

1/ ገበያው ሥርዓት ያልተከተለ ግብይትን እና የአቅም ገደብ ጥሰቶችን ለመከላከል ቢያንስ የሚከተሉትን ማዘጋጀት ይኖርበታል፦

ሀ) በአንድ ሰከንድ ውስጥ አንድ አባል ለመላክ የሚችለው የትዕዛዞች ቁጥር ገደብ፤

ለ) መዋዠቅን የመቆጣጠሪያ ዘዴ፤እና

ሐ) ቅድመ-ግብይት እና የድህረ-ግብይት ቁጥጥር፡፡

2/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ዓላማ ሲባል ገበያው የሚከተሉትን ማድረግ ይችላል፦

ሀ) ከማንኛውም አባል ወይም ድጋፍ ያለው ተሳትፎ ተጠቃሚ ስለድርጅቱ አደረጃጀት ዝግጅት፣ሥርዓት፣ የግብይት ቁጥጥር መረጃን መጠየቅ፤

ለ) የግብይት ሥርዓቱን የመጠቀም መብት በራሱ በገበያው አነሳሽነት፣ በአባሉ፣ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ወይም በባለሥልጣኑ ስልጣን በተሰጠው ማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት ሲጠየቅ በውስጠ-ደንባቸው የተደነገገ ከሆነ ወይም በባለሥልጣኑ ትእዛዝ ሲሰጥ፣ የግብይት ሥርዓቱን የመጠቀም መብትን ማገድ፤

ሐ) በአባላት ወይም ድጋፍ ባለው ተሳትፎ ተጠቃሚ የቀረቡ ያልተፈጸሙ ትዕዛዞችን ለመሰረዝ

የሚያስችል የግብይት ማስቆሚያ ዘዴን በሚከተሉት ሁኔታዎች ተግባራዊ ማድረግ፡-

i) በአባሉ ወይም ድጋፍ ባለው ተሳትፎ ተጠቃሚ ጥያቄ አባሉ ወይም ተጠቃሚው ያስገባቸውን ትዕዛዞች በሥርዓቱ ላይ መሰረዝ ካቃተው፤

ii)የትዕዛዝ መዝገቡ የተሳሳቱ የተደጋገሙ ትዕዛዞችን ከያዘ፤እና

iii) በገበያው ወይም በባለሥልጣኑ አነሳሽነት የተፈጸመ እግድ ሲኖር፡፡

መ) መዋዠቅን መቆጣጠሪያ ዘዴዎች ወይም የግብይት መድረክ ወይም ስርዓት አገልግሎቶች ብልሽት ሲያጋጥም ግብይቶችን መሰረዝ ወይም መሻር፤ እና

ሠ) ከአንድ በላይ የትዕዛዝ ማስገቢያ ሥርዓት በሚኖርበት ጊዜ በተለያዩ መግቢያዎች የገቡ ትዕዛዞችን ሚዛን በማስጠበቅ መቆራረጥ እንዳይኖር መከላከል መቻል፤

አለበት፡፡

3/ ገበያው የሚከተሉትን በተመለከተ ፖሊሲዎችን ማውጣት እና ዝግጅቶችን ማድረግ አለበት፡-

ሀ) መዋዠቅን የመቆጣጠርያ ዘዴዎች፤

ለ) ገበያው የሚጠቀምበትን የቅድመ-ግብይትና የድህረ-ግብይት መቆጣጠሪያዎችንና፣ አባላቱ ወደ መገበያያ ሥርዓቱ ለመግባት የሚያስፈልጋቸውን የቅድመ-ግብይትና ድህረ-ግብይት መቆጣጠሪያዎችን፤

ሐ) አባላት የራሳቸውን ግብይት የማቋረጫ ዘዴ ተግባራዊ የማድረግ ግዴታቸውን እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)(ሀ) መሠረት ለአባላት እና ድጋፍ ላለው ተሳትፎ ተጠቃሚ የመረጃ መስፈርቶችን፤

መ) የግብይት ሥርዓቱን የመጠቀም መብትን ማገድን፤

ሠ) የመሰረዝ ፖሊሲው ከትዕዛዞች እና ግብይቶች ጋር በተገናኘ የሚከተሉትን ያካትታል፡-

i) ጊዜን፤

ii) ሥነ-ሥርዓትን፤

iii) ሪፖርት የማቅረብ እና የግልጽነት ግዴታዎችን፤

iv) የአለመግባባት አፈታት ሥነ-ሥርዓቶችን፤እና

v) ስህተት ያለባቸው ግብይቶችን የመቀነሻ እርምጃዎችን፡፡

ረ) የሚከተሉትን የሚያካትት የትዕዛዝ አገባብ መቆጣጠሪያ ዘዴዎችን፦

i) አስቀድሞ በተወሰነ የጊዜ ገድብ ውስጥ በየአንድ ሰከንዱ ሊገቡ የሚችሉ የትዕዛዞችን ቁጥር፤

ii) የትዕዛዝ አገባብ መቆጣጠሪያ ዘዴው ለተወሰኑ አባላት የታለመ ካልሆነ በስተቀር በአባላት መካከል በእኩልነት የመስተናገድ ፖሊሲን፤እና

iii) የትዕዛዝ አገባብ መቆጣጠሪያ ዘዴ ተግባራዊ የተደረገበትን ክስተት ተክትሎ የሚወሰዱ እርምጃዎችን፡፡

4/ ገበያው በዚህ አንቀጽ የተገለጹትን ፖሊሲዎቹን እና ዝግጅቱን ለሕዝብ ይፋ ማድረግ አለበት፡፡ ሆኖም ይህ ግዴታ አስቀድሞ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ በየአንድ ሰከንዱ የሚሰጡ የተወሰነ ቁጥር ያላቸው ትዕዛዞችን በተመለከተ እንዲሁም መዋዠቅን ለመቆጣጠር የሚያገለግሉ ልዩ መስፈርቶችን አይመለከትም፡፡

5/ ገበያው ስርዓት ያልተከተሉ ግብይቶችን ለመከላከል የወሰዳቸውን እርማጃዎች በተሟላ የኤሌክትሮኒክ ማህደር በትንሹ ለአሥር (10) ዓመታት ጠብቆ ማቆየት አለበት፡፡

## 30. የግብይት መድረክ ወይም ሥርዓት በትክክል መሥራትን ስለመፈተሽ

1/ ገበያው የግብይት መድረኩን ወይም ሥርዓቱን ጥቅም ላይ ከማዋሉ ወይም ከማሻሻሉ በፊት በግልጽ የታወቁ የማበልጸጊያ እና የሙከራ ሥነ-ዘዴዎችን በመጠቀም ቢያንስ የሚከተሉትን ማረጋገጥ አለበት፦

ሀ) የግብይት ሥርዓቱ በታሰበለት ዓላማ መሠረት የሚሰራ መሆኑን፤

ለ) በግብይት ሥርዓቱ ውስጥ የተካተተው የሕግ ማስከበር እና የስጋት አስተዳደር ቁጥጥር ስርዓት እንደታሰበው የሚሰራ መሆኑን ጨምሮ የስህተቶችን ሪፖርት ለይቶ ማውጣት የሚችል መሆኑን፣ እና

ሐ) የግብይት ሥርዓቱ የሚያስተናግዳቸው የመልዕክቶች ቁጥር በከፍተኛ መጠን በሚጨምሩበት ጊዜም በብቃት መስራት መቀጠል የሚችል መሆኑን፡፡

2/ ገበያው የሚያስተዳድረው የግብይት መድረክ ወይም ሥርዓት የተዛባ የግብይት ሁኔታ እንዲፈጠር አሉታዊ አስተዋጽ እንደማይኖረው ለማረጋገጥ ሁሉንም ምክንያታዊ እርምጃዎች መውሰዳቸውን በባለሥልጣኑ በተጠየቀ በማንኛውም ጊዜ ማሳየት አለበት፡፡

## 31. የግብይት መድረክ ወይም ሥርዓት ላይ የሚደረግ ቀጣይነት ያለው ክትትል

1/ ገበያው ከሚከተሉት መስፈርቶች ጋር በተያያዘ የግብይት ሥርዓቱን አላባዎች ብቃት እና አጠቃቀም በቀጥታ የሚከታተል መሆኑን በባለሥልጣኑ በተጠየቀ በማንኛውም ጊዜ ማሳየት አለበት፦

ሀ) በአንድ ሰከንድ ውስጥ ከፍተኛውን መልዕክት የመቀበል አቅም አጠቃቀም በመቶኛ፤

ለ) ስርዓቱ በአንድ ሰኮንድ ውስጥ የተቀበላቸው፣ የተላኩ እና ውድቅ የተደረጉ መልዕክቶችን ጨምሮ አጠቃላይ የግብይት ሥርዓቱ የሚተዳደሩ የመልእክቶች ብዛት በግብይት ሥርዓቱ አሳባ ተደልድሎ፤

ሐ) በግብይት ሥርዓቱ ከማንኛውም ውጫዊ ማስተላለፊያ መልዕክት በመቀበል እና የማዛመጃ መሳሪያው በዚያው ማስተላለፊያ የመጀመሪያውን መልዕክት ባስተናገደበት እና ተያያዥ መልዕክት በላከበት መካከል ያለው የጊዜ ርዝማኔ፤እና

መ) የማዛመጃ መሳሪያው የአፈጻጸም ብቃት።

2/ ገበያው ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ክትትል በሚያደርግ ጊዜ በግብይት ሥርዓቱ ላይ ከተለዩ ችግሮች ጋር በተገናኘ ሁሉንም ተገቢ እርምጃዎች በቅደም ተከተል፣ በምክንያታዊነት በአፋጣኝ የግብይት ሥርዓቱን ለማስተካከል፣ ለማስቆም፣ ወይም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለመዝጋት የሚችል መሆን አለበት።

## 32. መዋዠቅን የማስተዳደሪያ መንገዶች

1/ ገበያው በግብይት ሰዓት ወቅት የግብይት ሥራን ራሱን በራሱ ለማቋረጥ ወይም ለማገድ የሚያስችሉ ሥርዓቶች ሊኖሩት ይገባል።

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 26 ላይ በተገለጸው መሠረት ግብይትን በጊዜያዊነት እንዲያቆም ወይም እንዲገድብ ባለሥልጣኑ ገበያውን ሊያዝ ይችላል።

3/ ገበያው የሚከተሉትን ማረጋገጥ አለበት:-

ሀ) የግብይት ዘዴዎቹ አቅምና አፈጻጸም በየጊዜው በሚገመገምበት ወቅት እና ከዚያም በኋላ ግብይትን ለማስቆም ወይም ለማገድ የሚያስችሉ ዘዴዎች ስራ ላይ ከመዋላቸው በፊት መፈተሻቸውን፤

ለ) ግብይትን ለማስቆም ወይም ለማገድ ስራ ላይ የሚውሉ ዘዴዎችን ለመቅረጽ፣ ለማደስ፣ እና ለመከታተል የሚችል ቴክኖሎጂ እና ብቃት ያለው የሰው ኃይል መመደቡን፤እና

ሐ) መዋዠቅ ማስተዳደሪያ ዘዴዎች ላይ የማያቋርጥ ክትትል መደረጉን።

4/ ገበያው መዋዠቅን እና ተያያዥ ለውጦች የሚያስተዳድርበትን ውስጠ-ደንቦቹንና የልኬት ዘዴዎቹን ከነማሻሻያቸው መመዝገብ እንዲሁም የዘዴውን አሰራር፣ አስተዳደር እና ማሻሻያዎቹን መዝግቦ መያዝ አለበት።

5/ ገበያው መዋዠቅን የማስተዳደሪያ ውስጠ-ደንቦቹ የግብይት ሥርዓቱ ለማስጠበቅ ሲባል በማኑዋል ሊስተካከል የሚችልበትን ሁኔታ የሚያስተናግድ የአሰራር ሥርዓት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

33. **<u>ቅድመ-ግብይትና ድህረ-ግብይት ቁጥጥር</u>**

1/ ገበያው በራሱ የግብይት መድረክ ወይም ሥርዓት ለተገበያየ ለእያንዳንዱ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ያወጣውን የቅድመ-ግብይት ቁጥጥር እንደሚከተለው መተግበር አለበት:-

ሀ) አስቀድሞ ከተቀመጠው መመዘኛ ጋር የማይጣጣሙ ትዕዛዞችን በቅደም ተከተላቸው መሠረት ወዲያውኑ የሚገደብ የዋጋ ጣራ እና ወለል፤

ለ) ከተለመደው ውጭ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውን ትዕዛዞች ወደ ትዕዛዝ መዝገብ እንዳይገቡ በራሱ የሚከላከል የከፍተኛ ትዕዛዝ ዋጋ፤ እና

ሐ) ከተለመደው ውጭ ከፍተኛ የሆነ መጠን ያላቸውን ትዕዛዞች ወደ ትዕዛዝ መዝገብ እንዳይገቡ በራሱ ሊከላከል የሚችል የከፍተኛ ትዕዛዝ መጠን አሰራር መዘርጋት፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱት የቅድመ-ግብይት መቆጣጠሪያዎች የሚከተሉትን በሚያረጋግጥ መልኩ መቅረጽ አለባቸው፡-

ሀ) በራሱ የሚሰራው መተግበሪያ በግብይት ክፍለ ጊዜም ሆነ በሁሉም ደረጃዎች በራሱ ገደቦችን የማስተካከል አቅም ያለው መሆኑን፤

ለ) ክትትል ማድረጊያው የሚዘገየው ከአምስት ሴኮንድ ለማይበልጥ ጊዜ መሆኑን፤

ሐ) ገደብን የሚያልፍ ትዕዛዝ ውድቅ የሚያደረግ መሆኑን፤እና

መ) ከሚመለከተው አባል ጥያቄ በቀረበ ጊዜ ከገደብ በላይ የሆኑ ትዕዛዞች ፈቃድ የሚያገኙበት አሰራርና ዝግጅት መኖሩን፤ እንደዚህ ዓይነት አሰራሮችና ዝግጅቶች ተፈጻሚ የሚደረጉት ከተወሰኑ ትዕዛዞች ወይም የትዕዛዞች ስብስቦች ጋር በተያያዘ በጊዜያዊነትና በልዩ ሁኔታ መሆኑን፡፡

3/ ገበያው ከአባላቱ የስጋት ግመገማ ስራ እንቅስቃሴዎች በመነሳት ተገቢ ነው የሚለውን የድህረ-ግብይት ቁጥጥር ማዘጋጀት አለበት፡፡

34. **<u>አነስተኛ የዋጋ እንቅስቃሴ መጠን</u>**

1/ ገበያው ለሁሉም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አነስተኛውን የዋጋ እንቅስቃሴ መጠን ስርዓት መተግበር አለበት፡፡

2/ አነስተኛ የዋጋ እንቅስቃሴ መጠን ሥርዓት የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን በተለያዩ ገበያዎች ሁሌም የመሸጥና የመግዛት እድል በበቂ መኖርን እና በጨረታ የሚጠየቁ አማካይ ዋጋዎች የሚያንጸባርቅ መሆን አለበት፡፡ እንዲሁም በምክንያታዊነት የተረጋጋ ዋጋ እንዲኖር የማስቻል አስፈላጊነትን እና ልዩነቱ ያላግባብ ገደብ

ሳይደረግ በቀጣይነት መጥበብን ከግምት ውስጥ ያስገባ እና ለእያንዳንዱ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ በተገቢ ሁኔታ የተዘጋጀ መሆን አለበት።

35. **የግብይት ሰዓቶችን ማቀናጀት**

1/ ማንኛውም ሪፖርት ሊደረግበት የሚችል ክስተት ቀን እና ሰዓት ለመመዝገብ የሚያገለግሉ የግብይት ሰዓቶች በግብይት መድረኮች ወይም ሥርዓቶች እና በአባላት ወይም ድጋፍ ባለው ተሳትፎ ተጠቃሚ መካከል ተመሳሳይ መሆን አለባቸው።

2/ ባለሥልጣኑ የግብይት ሰዓቶች በዓለም አቀፍ ደረጃዎች መሠረት የሚመሳሰሉበትን ትክክለኛነት የሚገልጽ የአሰራር ሥርዓት ሊያዘጋጅ ይችላል።

36. **ገበያ ስለመክፈት**

1/ ገበያው በሚያስተዳድርባቸው የግብይት መድረኮች ወይም ሥርዓቶች ላይ የገበያ ከፋችነት አገልግሎት ከሚሰጡ ከሁሉም አባላት ጋር የጽሁፍ ውል ሊኖረው ይገባል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው ስምምነት በቂ ቁጥር ካላቸው አባላት ጋር የተደረገ መሆኑን ገበያው ሊያረጋግጥ ይገባል።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደረገ ስምምነት፡-

ሀ) አባላቱ በማይለወጥ ሁኔታ ተወዳዳሪ የዋጋ ተመን እንዲያቀርቡ የሚጠይቁ፣ ውጤታቸው በመደበኛነት እና ተገማች በሆነ መልኩ ለገበያው ሁሌም የመሸጥና የመግዛት እድል በበቂ ሀኔታ እንዲኖር ማድረግ ሆኖ ይህ ዓይነት መስፈርት በዚያው የግብይት መድረክ ወይም ሥርዓት ለግብይቱ ልኬት እና ባህሪ ተገቢነት ያለው መሆን፤ እና

ለ) ቢያንስ የሚከተሉትን መግለጽ አለበት፡-

i) ሁሌም የመሸጥና የመግዛት እድል በበቂ ሀኔታ እንዲኖር የማድረግ የአባላቱን ግዴታዎች እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በገበያ ከፋችነት ውስጥ ከመሳተፍ የሚመነጭ ማንኛውም ሌሎች ግዴታዎችን፣ እና

ii) በመደበኛነት እና ተገማች በሆነ መልኩ ለገበያው ሁሌም የመሸጥና የመግዛት እድል በበቂ ሁኔታ እንዲኖረው ከገበያው ለአባሉ በተመላሽ ወይም በሌላ መልኩ የሚሰጥ ማንኛውም ማበረታቻ እና እንደዓግባብነቱ በሥርዓቱ ውስጥ ተሳታፊ በመሆኑ ምክንያት ለአባሉ የሚሰጥ ማንኛውንም ሌላ መብት።

4/ ገበያው በዚህ አንቀጽ የተጠቀሱትን የጽሁፍ ስምምነቶች ላይ ያሉ ግዴታዎች ተግባራዊ መሆናቸውን መቆጣጠር እና ማስፈፀም አለበት።

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን

5/ ገበያው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው የጽሁፍ ስምምነት ይዘት ወድያውኑ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ ያለበት ሲሆን በባለሥልጣኑ ሲጠየቅ እንደዓስፈላጊነቱ ተጨማሪ መረጃ ይሰጣል።

37. **ከግብይት መድረኮች ጋር ተያያዥነት ያላቸው የክፍያ መርሆዎች**

1/ ገበያው የሚከተሉትን ማረጋገጥ አለበት፦

ሀ) የግብይት ማስፈጸሚያ ክፍያ፣ ሌሎች ተጨማሪ ክፍያዎችን እና ተመላሽን ጨምሮ የክፍያ መዋቅሩ ግልፅ፣ ሚዛናዊ እና አድሎዓዊ ያልሆነ መሆኑን፤

ለ) ሥርዓት ያልተከተለ የግብይት ሁኔታ ወይም ገበያው እንዲጎዳ አስተዋፆ የሚያደርጉ ትዕዛዞችን መሠረዝ ወይም ግብይት እንዲከናወን፣ እንዲሻሻል ወይም እንዲሰረዝ ማበረታቻ የሚሰጥ አለመሆኑን ፤እና

ሐ) ለሚሰጡ ቅናሾች በምላሹ አንድን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ወይም አግባብነት ያላቸውን የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ስብስብ አስመልክቶ ገበያ የመክፈት ግዴታ የሚጥል መሆኑን።

2/ ለተሰረዙ ትዕዛዞች የሚከፈል ማንኛውም ክፍያዎች ትዕዛዙ በቆየበት የጊዜ ርዝማኔ መሰረት እና ክፍያዎችን ተፈጻሚ ከሚሆንበት ከእያንዳንዱ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ጋር የሚጣጣም መሆን አለበት።

3/ ገበያው በግብይት ሥርዓቱ አቅም ላይ የሚፈጠረውን ጫና ከግምት በማስገባት፤ ከተፈፀመ ትዕዛዝ ይልቅ ከተሰጠ በኋላ ለሚሰረዝ ትዕዛዝ፣ ከሚፈፀም ትዕዛዝ ይልቅ ከፍ ያለ የማይፈፀም ትዕዛዝ ወደ ግብይት ሥርዓቱ የሚያስገቡ አባላት እና ከፍተኛ ተደጋጋሚነት ያለው የግብይት ሥልተ-ቀመር በሚያከናውኑ ላይ ከፍ ያለ ክፍያ መጣል ይችላል።

38. **ስለዳታ ጥበቃ**

ገበያው በቁጥጥሩ ሥር የሚገኙትን ዳታና መረጃዎችን የሚጠብቅበት አሠራር መኖሩን ማረጋገጥ አለበት፤ ይህም አሰራር ተፈጻሚነት ካለው የዳታ ጥበቃ ሕግ ጋር የተጣጣመ መሆን አለበት።

39. **ስለቴክኖሎጂ እና ደህንነት**

1/ ገበያው ከስራ ክንውኑ ጋር በተያያዘ አግባብነት ያላቸውን ቴክኖሎጂ እና ደህንነትን የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚያስተዳደርበት እና ውሳኔ የሚሰጥበት ማዕቀፍ ማቋቋም አለበት። ይህ ማዕቀፍ፦

ሀ) እንደ የብቃት እቅድ እና ግምገማ፣ የቴክኖሎጂ ለውጦችን አስተዳደር ጉዳዮች ያሉ፤

ለ) ስር መንስኤዎችን ትንተናን ጨምሮ ክስተቶችን ማስተዳደርያ፤

ሐ) የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ እና ግንኙነት፣ ለክፋ የገበያ ሁኔታዎች የምላሽ ማዕቀፍ፤ እና

መ) የንግድ ቀጣይነት እቅዱን ማሻሻል እና ወቅታዊ ማድረግን፤

ማካተት አለበት።

2/ ገበያው የቴክኖሎጂውን ደህንነት፣ ምቹነት፣ እና ጤናማነት ለማረጋገጥ ተገቢ የሆኑ መሣሪያዎችንና አሠራሮችን መተግበር ያለበት ሲሆን እነዚህም አግባብነት ባላቸው የመንግስት ተቋማት የወጡ መስፈርቶችን የሚያሟሉ መሆን አለባቸው።

3/ ቴክኖሎጂው ጫናን የሚቋቋም፣ አስተማማኝ እና የተረጋጋ መሆኑን ለማረጋገጥ ገበያው ተገቢውን ዓለም አቀፍ ደረጃዎች የሚያሟላ ማዕቀፍ በማዘጋጀት በባለሥልጣኑ ያጸድቃል።

4/ ገበያው ቢያንስ በየዓመቱ ይህንን አንቀጽ ስለማክበሩ ለባለሥልጣኑ ማስረጃ ማቅረብ እና ይህም ባለሥልጣኑ በሚጠይቀው ቅጽ እና አቀራረብ መሠረት መሆን አለበት።

**40. <u>ስለንግድ ቀጣይነት</u>**

1/ ገበያው ውጤታማ የንግድ ሥራ ቀጣይነት ሥነ-ሥርዓቶችን እና ዝግጅቶችን ተግባራዊ ለማድረግ የንግድ ሥራ ቀጣይነት እቅድ ሊያወጣ እና ተገቢው የመጠባበቂያ ጣቢያ ሊኖረው ይገባል።

2/ የንግድ ሥራ እቅዱ ወሳኝ ስራዎች በሚቋረጡበት ጊዜ የሚያቋርጡ ክስተቶችን ማስተዳደርን ጨምሮ የግብይት ሥርዓቱን ወደ መጠባበቂያ ጣቢያ የማዘዋወር እና ከዚያ ጣቢያ ስራው የሚሠራበትን ዘዴ እና ወሳኝ የግብይት ዳታ መጠባበቂያ የመያዝ ሥነ-ሥርዓቶች እና ዝግጅቶችን ያካተተ መሆን አለበት።

3/ የንግድ ቀጣይነት እቅዱ ከግብይት ሥርዓቱ ጋር የተያያዙ የተለያዩ አሉታዊ ሁኔታዎችን የያዘ ሆኖ እነዚህም የግብይት ሥርዓቱን ጨምሮ የሰራተኞችን፣ የውጭ አቅራቢዎችን፣ የዳታ ማዕከላት አለመኖር እና ወሳኝ የሆኑ ዳታ እና ሰነዶች መጥፋትን ማካተት አለባቸው።

4/ የንግድ ቀጣይነት እቅዱ የንግድ እንቅስቃሴውን ለማስቀጠል የሚወስደውን ከፍተኛውን ጊዜ እና በሥርዓት ውስጥ ሊጠፋ የሚችለውን የዳታ መጠን የሚገልጽ ሆኖ ግብይቱን ሊያደናቅፍ የሚችል ክስተት በተፈጠረ ከሁለት ሰዓት ጊዜ ውስጥ ግብይት እንደገና መጀመር የሚያስችል እና በክስተቱ ምክንያት ሊጠፋ የሚችለው የዳታ መጠን ለዜሮ የተጠጋ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

5/ ገበያው በታቀደው መሠረት እንደሚሰራ ለማረጋገጥ የንግድ ቀጣይነት እቅዱን ለመፈተሽ፣ ለመገምገም እና ለማረጋገጥ ቀጣይነት ያለው ፕሮግራም ሊኖረው ይገባል።

6/ ገበያው የመቆራረጥ ስጋት እና ውጤቱን ለመለየት ቢያንስ በየአመቱ የተፅዕኖ ግምገማ ያካሂዳል።

7/ የተጽዕኖ ግምገማው ውጤት እና የንግድ ሥራ ቀጣይነት እቅዱን በቂነት በሚመለከት ማንኛውም ግኝቶች ለባለሥልጣኑ እና ለዳይሬክተሮች ቦርድ በወቅቱ ማሳወቅ አለበት።

8/ ገበያው በንግድ ቀጣይነት እቅዱ ውስጥ የግብይት ሥርዓት መቋረጡን በተመለከተ የተለዩትን ስጋቶች ከግምት ላለማስገባት የሚያደርገው ማንኛውም ውሳኔ በበቂ ሰነድ ተደግፎ እና በዳይሬክተሮች ቦርድ በግልጽ መጽደቅ አለበት።

9/ ገበያው የንግድ ሥራ ቀጣይነት ዕቅዱን በባለሥልጣኑ እንዲፀድቅለት ማቅረብ እና በዚህ አንቀፅ የተቀመጡትን መስፈርቶች ስለመፈጸሙ ቀጣይነት ያለው ግዴታዎች አካል ሆኖ ማስረጃዎችን ማቅረብ አለበት።

41. **<u>ስለአባላት ግምገማ</u>**

1/ የገበያው አባላት በአግባቡ ፈቃድ ያለው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ወይም በባለሥልጣኑ ለይቶ ያጸደቀው ማንኛውንም ሌላ ዓይነት ሰው እና በገበያው በሚተዳደረው የተወሰነ የገበያ ክፍል ውስጥ በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ለመገበያየት ተገቢ ነው ብሎ የገመተውን ያካተተ መሆን አለበት።

2/ ገበያው የወደፊት አባላቱን እና ድጋፍ ያለው ተሳትፎ ተጠቃሚዎቹን በማጥናት እና ሥነ-ሥርዓት በመዘርጋት ተገቢውን ጥናታዊ ግምገማ ያደርጋል።

3/ ገበያው ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ወይም በባለሥልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የአባላቱን እና ድጋፍ ያለው ተሳትፎ ተጠቃሚዎቹን ስጋት ተኮር ግምገማ ማድረግ አለበት።

4/ ስጋት ተኮር ግምገማው፡-

ሀ) አባላቱ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪነት የጸና ፈቃድ ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥን ጨምሮ የአባልነት መስፈርቶችንና ሁኔታዎችን ስለማክበራቸው የሚያካትት መሆን፤ እና

ለ) በእያንዳንዱ አባል እና እንደአግባብነቱ ድጋፍ ያለው ተሳትፎ ተጠቃሚ የተደረገው የግብይት መጠን እና ሊመጣ የሚችል ተጽዕኖ እንዲሁም ከመጨረሻው የስጋት ግምገማ የተደረገበትን ጊዜ ግምት ውስጥ ማስገባት፤

አለበት።

5/ ገበያው አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ሁሉ ተጨማሪ ግምገማዎችን ማከናወን አለበት።

6/ ገበያው የአባላቱን እና ድጋፍ ያለው ተሳትፎ ተጠቃሚዎችን ዝርዝር ለባለሥልጣኑ በመደበኛነት መስጠት አለበት።

7/ ገበያው ቢያንስ ለአስር(10) አመት የሚከተሉትን የኤሌክትሮኒክ ሰነዶች ይዞ መቆየት አለበት፡-

ሀ) ተገቢው ግምገማ የሚከናወንባቸው ሥርዓቶች እና ሁኔታዎች፤

ለ) ማዕቀቦችን እና የገንዘብ ቅጣቶችን ለመጣል የሚጠቀሙት መስፈርትና ስነ ሥርዓቶች፤

ሐ) የመጀመሪያ የተገቢነት ጥናት ግምገማ፤

መ) ዓመታዊ የስጋት ተኮር ግምገማ፤እና

ሠ) ዓመታዊ የአባላት ስጋት ተኮር ግምገማ ያላለፉ እና በእነሱ ላይ የተጣለው ማንኛውም ማዕቀብ።

## 42. ስለቴክኒካዊ እና ተግባራዊ የተስማሚነት ፍተሻ

1/ ገበያው የግብይት ሥርዓቱን ወይም መድረኩን ከማስጀመሩ ወይም ጉልህ ማሻሻያ ከማደረጉ በፊት ተገቢውን የግብይት መድረክ ወይም ሥርዓት ተደራሽነት የተስማሚነት እና የሕግ አክባሪነት እና የአባላቱን የግብይት ሥርዓት፣ ስልተ-ቀመር ወይም ስትራቴጂ ፍተሻ እንዲያካሂዱ መጠየቅ አለበት።

2/ የተስማሚነት ሙከራው የሚከተሉት መስራታቸውን ማረጋገጥ አለበት፦

ሀ) የአባላቶቹ የግብይት ሥርዓት ብቃት፣ ስልተ-ቀመር ወይም ስትራቴጂ ከገበያው የግብይት መድረክ ወይም ሥርዓት የማዛመድ ሥነ-አመክንዮ ጋር በሚጠበቀው ደረጃ መተሳሰር እና መጣጣሙን እንዲሁም ከውስጥ ወደ ውጪ እና ከውጪ ወደ ገበያው የመረጃ ፍሰት የማቀነባበር ብቃት ያለው መሆኑን፤

ለ) ትዕዛዝ ወደ ግብይት ሥርዓት ማስገባት፣ ማሻሻል ወይም መሰረዝ፣ ወይም ፍላጎት የማሳየት፣ ተለዋዋጭ ያልሆኑ የገበያ መረጃዎችን ከሥርዓቱ በቀላሉ የማውረድ እና ሁሉም የግብይት መረጃ ፍሰቶች የመሳሰሉ መሰረታዊ ስራዎች፤

ሐ) ለተወሰነ ጊዜ የሚሰጥ ትዕዛዝን ጨምሮ ግንኙነቱ አውታረ-መረቡን እና የዳታ መጥፋትን የሚቀንስ እና የዳታ ፍሰትን በቀጣይነት ለማረጋገጥ የዳታ ፍሰት መቆጣጠሪያ በተለዋዋጭ ሁኔታ የሚላመድ መሆኑን፤እና

መ) ማገገሚያው በቀን ውስጥ እንደገና ግብይት ማስጀመር እና የታገዱ ሰነዶችን ማስተላለፍን ወይም ወቅታዊ ያልሆነ የገበያ መረጃን ጨምሮ፣ የታገዱ ሰነዶችን በራሳቸው ቀድሞ በተወሰነላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንደገና ማንቃት እና የጎደሉትን መረጃዎች መሙላት።

3/ ገበያው ለአባላቱ እና ወደፊት አባል ሊሆኑ ለሚችሉ የተስማሚነት ሙከራ የሚያደርጉበትን ሁኔታ ማመቻቸት ያለበት ሲሆን የሙከራ አገልግሎቱ፦

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን

ሀ) በቀላሉ ተደራሽ የሆነና ከዋናው የግብይት ስርዓት ጋር የሚመሳሰል፤

ለ) አግባብ ባለው የግብይት አካባቢ ውስጥ የእያንዳንዱን የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች መደብ የሚወክሉ እና ሊፈተሹ የሚችሉ የሰነድ ሙዓለ ንዋዮችን ዝርዝር ማቅረብ የሚችል፤

ሐ) በአጠቃላይ በግብይት ሰዓት ወይም ከግብይት ሰዓት ውጪ ብቻ የሚገኝ ከሆነ አስቀድሞ በተዘጋጀ የጊዜ አባሪ መሠረት የሚሰጥ፤ እና

መ) በቂ እውቀት ባላቸው ሠራተኞች የሚታገዝ፤

መሆን አለበት።

4/ ገበያው፡-

ሀ) የተስማሚነት ሙከራ ምህዳሩ ከዋናው የግብይት አገልግሎት በሚገባ የተለየ መሆኑን ማረጋገጥ፤

ለ) አባላቶቹ እና ወደፊት አባል ሊሆኑ የሚችሉ የተስማሚነት ሙከራ መገልገያዎችን እንዲጠቀሙ ማድረግ፤ እና

ሐ) የተስማሚነት ሙከራ ውጤት ሪፖርት ለሙከራው አባላት ወይም የወደፊት አባላት እና በባለሥልጣኑ ሲጠየቅ ሪፖረቱን ማቅረብ፤

አለበት።

43. **<u>ስለግብይት ሥርዓት፣ ስትራቴጂ ወይም የስልተ-ቀመር ሙከራ</u>**

1/ ገበያው አባላቱ ወይም ተገቢ ሲሆን ድጋፍ ያለው ተሳትፎ ተጠቃሚ ስራ ላይ የሚያውሏቸውን የግብይት ዘዴዎች፣ ስትራቴጂዎቻቸው ወይም ስልተ-ቀመራቸው ስርዓት ያልተከተለ ገበያ እንዲፈጠር ወይም ለመፈጠሩ አስተዋፆ እንዳያደርግ ለመከላከል ሙከራ ያደረጉ መሆናቸውን ማረጋገጫ እንዲሰጡ ማድረግ አለበት።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ሙከራ የግብይት ዘዴውን፣ ስትራቴጂ ወይም ስለተ-ቀመሩን ተግባራዊ ከመደረጉ ወይም መሠረታዊ ማሻሻያ ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት መከናወን አለበት።

3/ ገበያው ለአባላቱ የሚከተሉትን የያዘ የሙከራ ማድረጊያ ምህዳር መስጠት አለበት፡-

ሀ) ሥርዓት ያልተከተለ የግብይት ሁኔታን ጨምሮ በተቻለ መጠን ከትክክለኛ ገበያ ጋር የሚመሳሰሉ የመሞከርያ መገልገያ፤እና

ለ) አባላቱ የተለያዩ ሁኔታዎችን እንዲሞክሩ የሚፈቅድ፤ ለግብይት እንቅስቃሴያቸው ያስፈልጋል ብለው የሚገምቷቸውን ሥራዎችን፣ ፕሮቶኮሎችን እና መዋቅሮችን የያዘ።

**44. <u>የገበያው ውስጠ-ደንቦች - ጠቅላላ</u>**

1/ ገበያው አባላቱ ሊከተሉ የሚገባቸውን የስነ-ምግባር ውስጠ-ደንቦች በማውጣት እና በማስከበር አባላቱን ይቆጣጠራል፡፡

2/ ገበያው የቁጥጥር ወይም የክትትል ተግባራት ባሉት ጉዳዮች ጋር በተገናኘ ውስጠ-ደንብ ያወጣል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከቱ ውስጠ-ደንቦች በውክልና ከተሰጠው ስልጣን ጋር በተያያዘ ማዕቀቦች እና የዲሲፕሊን ስልጣን ውስጠ-ደንቦችን፣ የግጭት አፈታት ሥነ-ሥርዓት እና ሊፈጠሩ የሚችሉ የጥቅም ግጭቶች የሚፈቱበት ሥነ-ሥርዓቶች እና ህግን እና ደንቦችን ለመመርመር እና ለማስከበር ከባለስልጣኑ ጋር ትብብር ስለማድረግ፣ እና የምዝገባ መስፈርቶችን የሚያስተዳድሩ ወይም የሚመለከቱ ውስጠ-ደንቦችን ያካትታል፡፡

**45. <u>ስለአባልነት ውስጠ-ደንቦች</u>**

1/ ገበያው የግብይት መድረኩ ወይም ሥርዓቱ አባልነትን አስመልክቶ መሟላት ያለባቸውን መስፈርቶችና ሁኔታዎች በማዘጋጀት በባለሥልጣኑ ማስጸደቅ አለበት፡፡

2/ ገበያው የሚከተሉትን የሚገልጽ በሁሉም አባላት ላይ ተፈጻሚ የሚሆን የሥነ-ምግባር ደንቦች ማዘጋጀት አለበት፡-

ሀ) የአባላቱን ሥነ-ባህርይ ደረጃዎች፤

ለ) በአዋጁ ክፍል 12 ላይ የተደነገጉትን የተከለከሉ የግብይት ተግባራትን አለመፈጸምን ጨምሮ የገበያ ሥነ-ምግባር መስፈርቶች፤

ሐ) ሕግ በማያከብር አባል ላይ ማዕቀቦች ወይም ቅጣቶች የሚጣሉባቸውን መስፈርቶችና ሥነ-ሥርዓቶች፤ እና

መ) የግብይት መድረኩን ወይም ሥርዓቱን የመጠቀም መብት ሊታገድና አባልነት ሊታጣ የሚችልባቸውን ሁኔታዎች፡፡

**46. <u>የግብይት መድረኩን ወይም የሥርዓቱን ተደራሽነት የሚመለከቱ ውስጠ-ደንቦች</u>**

1/ ገበያው አግባብነት ያለውን የግብይት መድረክ ወይም ሥርዓት ተደራሽነት የሚገዙ ውስጠ-ደንቦችን በባለሥልጣኑ አጸድቆ ማውጣት እና ተግባራዊ ማድረግ ያለበት ሲሆን እነዚህም፡-

ሀ) ግልጽና ከአድልዎ የጸዱ፤

ለ) በተጨባጭ መሥፈርቶች ላይ የተመሠረቱ፤እና

ሐ) ለኢንቨስተሮች ጥበቃና የገበያውን መልካም ስም ለማስጠበቅ፤ አስፈላጊ የሆኑ ድንጋጌዎችን የሚያካትቱ፤

መሆን አለባቸው፡፡

2/ ከላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር የተጠቀሱት ውስጠ-ደንቦች ከሚከተሉት የሚመነጩ ማናቸውንም የአባላት ግዴታዎችን መግለጽ አለባቸው፡-

ሀ) ከሕግና ከቁጥጥር መስፈርቶች፤

ለ) በገበያው ወይም በገበያው ክፍል ላይ ከሚደረጉ ግብይቶች ጋር ከሚገናኙ ውስጠ-ደንቦች፤እና

ሐ) በግብይት መድረኩ ወይም በግብይት ሥርዓቱ ላይ የሚፈጸሙ ግብይቶችን ክፍያ ማጣራትና መፈጸምን ከሚመለከቱ ውስጠ-ደንቦችና ሥርዓቶች።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሱት ውስጠ-ደንቦች አባሉ ለደንበኞቹ አግባብነት ያለውን የግብይት መድረክ ወይም ሥርዓት በቀጥታ በኤሌክትሮኒክ መሳሪያ እንዲሳተፉ ስለማስቻሉና ይህም ሲሆን በደንበኞቹ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ ሁኔታዎችን መግለጽ አለበት።

## 47. በቀጥታ በኤልክትሮኒክ መሳሪያ ስለመሳተፍ

1/ ገበያው በግብይት መድረኩ ወይም ሥርዓቱ ለብቁ ሰዎች በቀጥታ በኤሌክትሮኒክ መሳሪያ መሳተፍ የሚፈቅድ ከሆነ ውጤታማ የሆነ የቁጥጥር ሥነ ሥርዓቶች፣ አሰራሮች እና ዝግጅቶች ሊኖሩት የሚገባ ሲሆን ይህም አባላት ይህን አገልግሎት በዚህ መመሪያ በተቀመጠው አግባብ ብቻ እንደሚጠቀሙ ማረጋገጥ ይኖርበታል።

2/ ማንኛውም በቀጥታ በኤሌክትሮኒክ መሳሪያ ለመሳተፍ የተሰጠ ፈቃድ፡-

ሀ) የመሳተፍ ፈቃድ ሊሰጣቸው የሚችሉ ሰዎችን ብቁነት በተመለከተ የተቀመጠ ተገቢ መስፈርቶች ያለው መሆን፤እና

ለ) የብቃት መስፈርቶቹ ብቁ የተባሉት ሰዎች መደበኛ ኢንቨስተሮች፣ ተቋማዊ ተሳታፊዎች ወይም ብቁ ኢንቨስተሮች መሆን አለመሆናቸው ጋር በተያያዘ ሆኖ የኢንቨስተሮችን ጥበቃ ግዴታዎችን ለመተግበር ያለመ መሆን፤

አለበት።

3/ አባላት በዚህ መመሪያ የተቀመጡ መስፈርቶች ጋር በተገናኘ የቀጥታ በኤሌክትሮኒክ መሳሪያ መሳተፍን በመጠቀም ለሚተላለፉ ትዕዛዞች ወይም ለሚፈጸሙ ግብይቶች ኃላፊነታቸው የተጠበቀ መሆኑን ገበያው ማረጋገጥ ይኖርበታል።

4/ ገበያው በዚህ መንገድ የሚደረጉ ግብይቶችን የሚመለከቱ ተገቢ የቴክኖሎጂ የስጋት ቁጥጥርና ገደቦችን ማዘጋጀት እንዲሁም በቀጥታ በኤልክትሮኒክ መሳሪያ በመሳተፍ ወደ ግብይት ሥርዓቱ የሚገቡ

ትዕዛዞችን ወይም ግብይቶችን በአባላት ከሚደረጉ ትዕዛዞች ወይም ግብይቶች መለየትና አስፈላጊ ሲሆን ማስቆም መቻል አለበት፡፡

5/ ገበያው በአባሉ እና በደንበኛው መካከል የቀጥታ በኤሌክትሮንክ መሳሪያ መሳተፍ ፈቃድ መስጠትን አስመልክቶ አስገዳጅ ሕጋዊ ስምምነት የሚፈልግ እና አንድ አባል ለደንበኛው የሚሰጠውን በቀጥታ በኤሌክትሮኒክ መሳሪያ የመሳተፍ ፈቃድ በተመለከተ ለዚህ አንቀጽ ተገዢ በማይሆንበት ጊዜ የሚታገድበት ወይም የሚቋረጥበትን አሠራር መዘርጋት አለበት፡፡

48. **ስለግብይት ውስጠ-ደንቦች**

1/ ገበያው ለግብይት ሥርዓቶቹ እና መድረኮቹ ግልጽና የማያወላዱ ውስጠ-ደንቦችን እና ሥነ-ሥርዓቶች አዘጋጅቶ በባለሥልጣኑ ማስጸደቅ ያለበት ሲሆን ውስጠ-ደንቦቹ ፍትሐዊና ትክክለኛ ግብይት እንዲከናወን የሚያስችሉ እና በተቀላጠፈ መንገድ ትዕዛዞች የሚፈጸሙባቸውን ተጨባጭ መስፈርቶች ማቋቋም አለባቸው፡፡

2/ የገበያው አባላት ደንበኞቻቸውን በመወከል እና ትዕዛዞቻቸውን በግብይት መድረኮች ወይም ሥርዓቶች ላይ በሚፈጽሙበት ጊዜ የኢንቨስተር ጥበቃ ግዴታዎችን አክብሮ የመስራት ኃላፊነት ይጠበቅባቸዋል፡፡

49. **ስለኮሎኬሽን**

የገበያው የኮሎኬሽን አገልግሎት ውስጠ-ደንቦች ግልጽ፣ ፍትሃዊ እና ከአድልዎ የጸዳ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

50. **ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ ወይም ቅበላ የሚመለከቱ ውስጠ-ደንቦች**

1/ ገበያው በአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (40) መሠረት የሚከተሉትን የሚያሟላ የምዝገባ መስፈርቶች አዘጋጅቶ በባለሥልጣኑ ያስጸድቃል፡-

ሀ) ግልጽ እና ግልጽኝነት ያለው፤እና

ለ) ወደ ግብይት ቅበላ የተደረገላቸው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ፍትሐዊ፣ ትክክለኛና ቀልጣፋ በሆነ መንገድ ግብይት ሊደረግባቸው የሚችሉ መሆናቸውን የሚያረጋግጡ፤

ውስጠ-ደንብ ሊኖረው ይገባል፡፡

2/ ተዛማጅ ሰነደ ሙዓለ ንዋይን በተመለከተ የምዝገባ መስፈርቱ የተዛማጅ ውሎች አዘገጃጀት ትክክለኛ የዋጋ ትመና እንዲሁም ውጤታማ የክፍያ ሁኔታዎች መኖራቸውን የሚፈቅድ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

3/ ገበያው በዚህ አንቀጽ በተገለጸው መሰረት ለምዝገባ እና ለግብይት ቅበላ ስራ በቂ የቴክኒክ እውቀት ያለው ተገቢ የሰው ኃይል የተመደበ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

4/ ገበያው ውጤታማ ዝግጅቶችን በማደራጀት እና በመዘርጋት፡-

ሀ) በግብይት መድረኩ ወይም ሥርዓቶቹ ላይ ለመመዝገብ ወይም በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ለመገበያየት

ፈቃድ ለማግኘት የሚፈልግ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አውጪ በገበያው የተዘጋጁትን ውስጠ-ደንቦች እንደሚያሟላ እና አክብሮ እንደሚሰራ ማረጋገጥ፤እና

ለ) የአውጪውን እንደዚህ ያሉ ውስጠ-ደንቦች በቀጣይነት ማክበርን በመደበኛነት መገምገም፤

አለበት፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት የሚደረገው የማረጋገጥ ሥራ ቢኖርም ገበያው፡-

ሀ) ለመመዝገብ ወይም ወደግብይት ቅበላን ለማጽደቅ በቅድሚያ የባለሥልጣኑን የጽሁፍ ማረጋገጫ ማግኘት፤ እና

ለ) የምዝገባ ወይም ወደግብይት ቅበላ ማመልከቻ ውድቅ ለማድረግ ወይም ለመከልከል የሚወስደውን ማንኛውንም ውሳኔ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ፤

አለበት፡፡

6/ ገበያው በአዋጁ አንቀጽ 77 በተመለከተው መሠረት በሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪው የሚሰጡ ወሳኝነት ያላቸው መረጃዎችን ማግኘት የሚቻልበትን ሥርዓቶችን መዘርጋት አለበት፡፡

## 51. <u>የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ከምዝገባ ወይም ከግብይት ስለመታገድ እና መነሳት</u>

1/ የባለሥልጣኑ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ከግብይት እንዲታገድ ወይም እንዲሰረዝ የማስደረግ ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ገበያው ከባለሥልጣኑ እገዳውን ወይም ስረዛውን የማይቃወም መሆኑን ቅድሚያ የጽሁፍ ማረጋገጫ ሲያገኝ አግባብነት ያላቸውን ውስጠ-ደንቦች የማያሟላ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ምዝገባ ወይም ግብይት ማገድ ወይም መሰረዝ ይችላል፡፡

2/ የአንድ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ከምዝገባ ወይም ከግብይት መታገድ ወይም መሰረዝ የእገዳውን ወይም የስረዛውን ዓላማ ለማገዝ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ከዚሁ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ጋር የሚገናኙ ወይም የሚጠቀሱ ተዛማጅ ውሎችም እንዲታገዱ ወይም እንዲሰረዙ የሚያስገድድ መሆን አለበት፡፡

3/ ገበያው ማንኛውንም ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ወይም ግንኙነት ያለውን ተዛማጅ ውል መታገድ ወይም ስረዛ ወዲያውኑ ለሕዝብ ይፋ ማደረግ አለበት፡፡

## 52. <u>ስለክትትል እና ቅኝት</u>

1/ ገበያው አባላቶቹ ውስጠ-ደንቦቹን እንዲያከብሩ በመደበኛነት ክትትል ለማድረግ ውጤታማ አደረጃጀቶችን እና ሥነ-ሥርዓቶችን ያዘጋጃል፣ ይይዛል፡፡

2/ ገበያው የሚከተሉትን ለመለየት የሚላኩ ትዕዛዞችን፣ የተሰረዙ ትዕዛዞችን ጨምሮ በአባሎቹ የሚፈጸሙ ግብይቶችን መከታተል አለበት፡-

ሀ) የገበያው ውስጠ-ደንቦች ጥሰቶችን፤

ለ) ሥርዓት ያልተከተሉ የግብይት ሁኔታዎችን፤

ሐ) በዚህ መመሪያ ወይም በአዋጁ መሰረት የተከለከሉ ባህሪያትን ሊያመለክት የሚችል ድርጊት፤እና

መ) ከሰነደ ሙዓለ ንዋይ ጋር በተያያዘ የግብይት ሥርዓት መቋረጥን።

3/ ገበያው፦

ሀ) የተጠለፉ ሥርዓት ያልተከተሉ ግብይትቶችን ጨምሮ የክትትል እና የቅኝት ተግባራትን አጠቃላይ የኤሌክትሮኒክስ መዝገቦችን መያዝ፤ እና

ለ) በዚህ አንቀጽ ሥር የተጠቀሱትን ተግባራት ለማከናወን የሚያስፈልጉ ሀብቶችን መመደቡንና ማቅረቡን ማረጋገጥ፤

አለበት።

53. **ስለምርመራ እና የዲሲፕሊን እርምጃ**

ገበያው በአዋጁ ድንጋጌዎች መሠረት እንዲሁም በዚህ መመሪያ እና ይህን መመሪያን በመከተል ባወጣቸው ውስጠ-ደንቦች መሠረት የሚወስዳቸውን ማንኛውንም የዲሲፕሊን እርምጃ ወዲያውኑ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለበት።

54. **ቀጣይነት ስላላቸው ግዴታዎች**

1/ ገበያው የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች በማክበር እየሠራ መሆኑን የሚገልጽ ማረጋገጫ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ወይም በተደጋጋሚ ባለሥልጣኑ በሚወስነው መሠረት ማቅረብ አለበት።

2/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ዓላማ ገበያው የሚከተሉትን የሚያካትት መረጃ፣ መደበኛ ሪፖርቶችና ግምገማዎች በዚህ መመሪያ በተገለጸው መሠረት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፦

ሀ) በገበያው ሊከናወኑ ከታሰቡት አገልግሎቶችና ተግባራት አንጻር የሚፈለግን ማንኛውንም የካፒታል ማሻሻያን ጨምሮ በአንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ (7) መሠረት የፋይናንስ የስጋት ምዘናና የፋይናንስ ሪፖርትን፦

ለ) በአንቀጽ 18 መሠረት የአስተዳደር መዋቅሮች ግምገማን፤

ሐ) በአንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ (6) መሠረት የስጋት እና የህግ ማስከበር ሪፖርቶችን፤

መ) በአንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት የመገበያያ መድረክ ወይም ሥርዓት አቅም ሪፖርትን፤

ሠ) በአንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የትዕዛዝ መዝገብ መረጃን፤

ረ) በአንቀጽ 28 መሠረት የመገበያያ መድረኩ ወይም የሥርዓቱ ቁጥጥሮችና ሌሎች ስርዓቶች ምዘናን፤

ሰ) በአንቀጽ 30 እና 31 መሠረት ከግብይት መድረኩ ወይም ሥርዓቱ ሙከራና ቀጣይ ክትትል ጋር የሚገናኙ ግኝቶችና እርምጃዎችን፤

ሸ) በአንቀጽ 39 መሠረት የቴክኖሎጂና ደህንነት መስፈርቶች መከበራቸውን የሚያሳይ ማስረጃ፤

ቀ) በአንቀጽ 40 መሠረት የንግድ ቀጣይነት ዝግጅት መስፈርቶች የተሟላ ስለመሆኑ ያለውን የሕግ አክባሪነት ማስረጃ፤

በ) በአንቀጽ 41 መሠረት የአባላት ወይም የተሳታፊዎች ዝርዝር እና የአባልነት ስጋት ምዘናን፤

ተ) በአንቀጽ 44 መሠረት በገበያው ውስጠ-ደንቦች ላይ የሚደረጉ ማንኛውም ለውጦች ወይም ማሻሻያዎች፤ እና

ቸ) በየጊዜው ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ናቸው የሚላቸው ማንኛውም ሌሎች መረጃዎች፡፡

55. **ለባለሥልጣኑ ሪፖርት እና እገዛ ስለማድረግ**

1/ የዚህ መመሪያ አንቀፅ 54 እንደተጠበቀ ሆኖ ገበያው የሚከተሉትን መረጃዎች ሲጠየቅ በባለሥልጣኑ በሚጠይቀው አቀራረብ እና ቅጽ መሠረት ማቅረብ ይኖርበታል፦

ሀ) የዕለት ተዕለት ግብይት በዋጋ እና በመጠን፣ ተግባራቱን፣ አዝማሚያዎችን፣ ልማዶች እና ምልከታዎችን ጨምሮ በገበያው የግብይት መድረክ ወይም ሥርዓቶች ላይ በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች መገበያየት ጉዳዮችን የተመለከተ መረጃ፤

ለ) መልስ ያላገኙ የመሸጥ ወይም የመግዛት ግብዣዎች ወይም ባልተጠናቀቁ ግብይቶች የሚከሰቱ ያልተከፈሉ እዳዎች በገበያው ሊያስከትሉ የሚችሉት ስጋት የሚመለከቱ የስጋት አስተዳደር ሪፖርቶች፣ ወይም ገበያው የሚጠቀምባቸውን የክፍያ ማጣራት እና መፈጸም ስራ ዝግጅቶችን የሚመለከቱ መረጃዎችን፤

ሐ) ከሥርዓት ያልተከተለ የግብይት ሁኔታዎች ወይም የሥርዓት መቋረጥ ጋር የተያያዙ ሪፖርቶች፤

መ) የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን መመዝገብ እና ከምዝገባ መሰረዝ መከታተል እና በቀጣይ የምዝገባ መስፈርቶችን ማክበርን ጨምሮ ከምዝገባ ወይም በሰነደ ሙዓለ ንዋይ መገበያየት ሥራ ጋር የተገናኘ

መረጃ፤

ሠ) የገበያ ሥነ-ምግባር እና የቅኝት ግኝቶች፤

ረ) የምርመራ እና የዲሲፕሊን እርምጃዎች መረጃ፤ እና

ሰ) በባለሥልጣኑ ለገበያው በውክልና የተሰጡ ተግባራትና ሥልጣንን የሚመለከቱ ሌሎች ጉዳዮች።

2/ በአዋጁ አንቀጽ 37 ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) መሠረት ገበያው እና ቦርዱ ተገቢውን መረጃ በሃያ አራት (24) ሰዓት ውስጥ በማቅረብ እና በገበያው ላይ ወይም በኩል የሚደረጉ የተከለከሉ የግብይት ተግባራት ለመመርመርና ለመክሰስ ለባለሥልጣኑ ሙሉ እገዛ ማድረግ አለባቸው።

**56. የሂሳብ ሪፖርቶችን ለባለሥልጣኑ ስለማቅረብ**

1/ ገበያው በኢትዮጵያ የሒሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ በተቀመጠው የሂሳብ አያያዝ እና ኦዲት ደረጃ መሰረት የሚከተሉትን የሂሳብ መግለጫዎች በማዘጋጀት ለባለሥልጣኑ ያቀርባል፦

ሀ) ሩብ ዓመቱ በተጠናቀቀ በሠላሳ (30) ቀናት ውስጥ የሩብ ዓመት የሂሳብ መግለጫ፤

ለ) የሂሳብ ዓመቱ በተጠናቀቀ በአራት(4) ወር ውስጥ ኦዲት የተደረጉ ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫዎች፤ እና

ሐ) በባለሥልጣኑ በሚገለጸው የጊዜ ገደብ መሠረት ማንኛውንም ወቅታዊ የሂሳብ ሪፖርት።

2/ ኦዲት የተደረገ የሂሳብ መግለጫዎች በአዋጁ አንቀጽ 63 መሠረት በኢትዮጵያ የሒሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ፈቃድ የተሰጠው እና በባለሥልጣኑ የጸደቀ የውጭ ኦዲተር የሚሰጠውን አስተያየት በሚከተሉት ላይ ማካተት አለበት፦

ሀ) በዚህ መመሪያ መሰረት የተቀመጡ የካፒታል መመዘኛዎችን የተሟሉ ስለመሆኑ፤

ለ) በገበያው ቀጣይ ሁኔታ ማለትም በውጭ ኦዲተሩ አስተያየት በሂሳብ መዛግብቱ ላይ በሚታየው መሠረት ባለፈው የሒሳብ ዓመት ከተደረገው ግብይት ዓይነትና መጠን አንጻር ገበያው ያለበት የገንዘብ ቁመና ሥራውን ሊያስቀጥል በሚያስችለው ሁኔታ መሆኑን፤እና

ሐ) ሂሳቦቹ ትክክለኛ ያልሆኑ መግለጫዎችን መያዝ አለመያዛቸውን።

3/ ገበያው ኦዲት በተደረጉ የሂሳብ መግለጫዎቹ ውስጥ ከካፒታል ውስጥ አምስት በመቶ (5%) እና ከዚያ በላይ የያዙ ባለ አክሲዮኖች ዝርዝር መግለጽ አለበት።

## ክፍል ሦስት

## ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ

### 57. ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ፈቃድ መስፈርቶች

1/ ለያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ፈቃድ የሚቀርብ ማመልከቻ ባለሥልጣኑ የመመሪያውን የዚህን ክፍል ግዴታዎች ለማክበር በቂ ዝግጅት መደረጉን ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች በሙሉ ማካተት አለበት፡፡

2/ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ፈቃድ የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-

ሀ) የተቋሙ እና ድርጅቱ መዋቅር መግለጫ፣ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ፈቃድ ከሚፈልግ ድርጅት ባለአክሲዮኖቹ ዝርዝር መግለጫ ጋር፤

ለ) ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት እጩነት የሚያቀርባቸውን ሰዎች ዝርዝር ከእያንዳንዳቸው የትምህርት ማስረጃ እና የሥራ ልምድ የሚያሳይ መግለጫ ወይም አጭር ተመሳሳይ መግለጫ፤

ሐ) ከፍተኛ የሥራ ኃላፊነት እና የሕግ ማስከበር ኃላፊነት ያላቸውን ሰዎች ጨምሮ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ የአመራር መዋቅሩን ዝርዝር መግለጫ፤

መ) ፈቃድ ያለው ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ የዳይሬክተሮች ቦርድ እና ከፍተኛ ባለሙያዎች በባለሥልጣኑ በሚወስነው መሠረት በባለሥልጣኑ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች የፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር መመርያ ላይ የተመለከቱትን የብቁነት እና ተገቢነት መስፈርቶች ማሟላታቸውን፤

ሠ) በባለሥልጣኑ የወጡትን የሚመለከታቸው የድርጅት አስተዳደር ማስታወቂያዎችን፣ አቅጣጫዎችን ወይም መመሪያዎችን ማክበር፤

ረ) የፋይናንስ ሰነዶችን ባህሪ እና አይነት እና የሚገበያዩ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን እና ተያያዥነት ያላቸውን ኢንቨስተሮች መደብ ጨምሮ በገበያው የታቀደው የአሠራር አጠቃላይ መግለጫ፤

ሰ) የተመዘገበ ሰው ለመሆን የሚያበቁ መስፈርቶች እና ብቁነቱ የሚገመገምበት የተገቢነት ሥርዓቶች፤

ሸ) የግብይት አገልግሎት ወይም መድረክ በአጠቃላይ የዋጋ ተመን ሥርዓት የሚባለውን አጠቃላይ መግለጫ እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 61 የተገለጹትን መረጃዎች፤

ቀ) የታቀደ የስጋት አስተዳደር፣ የክፍያ እና ርክብክብ ስርዓት እንዲሁም ማንኛውም እውቅና ከተሰጠው

ማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት ጋር ስለ የሚኖረው መስተጋብር ዝርዝር፤

በ) በሥራ ላይ ያሉት የዳታ ጥበቃ፣ የሳይበር ደህንነት እና የንግድ ሥራ ቀጣይነት ዘዴዎችና አደረጃጀቶች እና በሚመለከታቸው የመንግስት ኤጀንሲዎች የሚወጡትን መስፈርቶች ማክበራቸውን የሚያሳዩ ተገቢነት ያላቸው ደጋፊ ማስረጃዎች መግለጫ፤

ተ) የተሰነደ የንግድ ቀጣይነት እና የማገገሚያ እቅድ፤

ቸ) የታቀደው የክትትል እና ቅኝት ዝግጅቶች ዝርዝሮች፤እና

ነ) ባለሥልጣኑ የሚጠይቃቸው ሌሎች መስፈርቶች።

3/ አመልካቹ የዋጋ ተመን ሥርዓቱን የሚከውኑ፣ የሚጠቀሙ እና ሳይቋረጥ የሚያስቀጥሉ ሰዎችን መለየት አለበት።

## 58. ስለዝቅተኛ የተከፈለ ካፒታል መስፈርት

1/ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ፈቃድ ለማግኘት የሚያስፈልገው ዝቅተኛ የተከፈለ ካፒታል ብር 25,000,000 (ሃያ አምስት ሚሊዮን ብር) መሆን አለበት።

2/ ባለሥልጣኑ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያው ባህሪ እና የሥራ መጠን እንዲሁም ሌሎች ተገቢ የስጋቶችን ታሳቢ በማድረግ ዝቅተኛ የካፒታል መስፈርት በየጊዜው እንዲሻሻል ሊያዝ ይችላል።

3/ ባለሥልጣኑ የታቀደ የዝቅተኛ ካፒታል መስፈርት ማንኛውም ማሻሻያ ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ እና በጽሁፍ ለላልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ፈቃድ ያገኙ ማሳወቅ ይኖርበታል።

4/ በመመስረቻ ጽሁፉ እና እንደአግባቡ በንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀቱ ላይ የተመለከተው የካፒታል መጠን በዚህ አንቀጽ መሰረት ዝቅተኛውን የተከፈለ ካፒታል ጋር እኩል ወይም የሚበልጥ መሆን አለበት።

5/ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ የሚከተሉትን ለመስራት የሚያስችሉት በቂ የጥሬ ገንዘብ እና ገንዘብ-አከል ሀብት የሚያካትት የካፒታል ሊኖረው ይገባል:-

ሀ) ማንኛውንም የካፒታል ወጪ እና የስራ ማካሄጃ ወጪን ጨምሮ አሁን እያከናወነ ያለውን እና ያቀዳቸውን ሥራዎችና ክንውኖች ለማስቀጠል የሚያስችል፤

ለ) የተገመገሙትን የስጋት ሁኔታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት ቢያንስ የአንድ አመት የወደፊት ጊዜን ለመሸፈን፤ እና

ሐ) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያውን በአግባቡ ለመቀነስ ወይም ለመዝጋት የሚያስችል።

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (5) የተገለጸው ቢኖርም ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያው ጥሬ ገንዘብ እና ገንዘብ-አከል ሀብት የጠቅላላ ሀብቱን ቢያንስ አርባ በመቶ (40%) መሆን አለበት፡፡

7/ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያው በማንኛውም ጊዜ የዚህን አንቀፅ መስፈርቶች አሟልቶ መገኘት ያለበት ሲሆን ለያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ፈቃድ በሚያመለክትበት ጊዜም ሆነ በቀጣይነት ለባለሥልጣኑ ሪፖርት ለማቅረብ ባለበት ግዴታ መሠረት የዚህን አንቀፅ መስፈርቶች የሚያሟላ ስለመሆኑ የፋይናንስ ስጋት ምርመራ እና የፋይናንስ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

## 59. ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ፈቃድ

በዚህ መመሪያ መሰረት የተገኘ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ፈቃድ የሚከተሉትን የሚገልጽ መሆን

አለበት፡-

1/ በተሰጠው ፈቃድ ለመገበያየት የሚፈቀደው የገንዘብ ሰነዶች ዓይነት፤

2/ በሚመለከታቸው የሰነደ መዓለ ንዋይ ለመገበያየት የተፈቀደላቸው የሚመለከታቸው ኢንቨስተሮች መደብ፤ እና

3/ በባለሥልጣኑ የተደነገጉ ማናቸውም ገደቦች ወይም ልዩ ሁኔታዎች፡፡

## 60. ስለተመዘገቡ ሰዎች

1/ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያውን የመጠቀም መብት ለተመዘገቡ ሰዎች ብቻ የተገደበ ሲሆን፡-

ሀ) ከባለሥልጣኑ ተገቢውን ፈቃድ ያላቸው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች፤ ወይም

ለ) አግባብ ባለው ገበያ ውስጥ የሰነደ መዓለ ንዋዮችን ለመግዛት፣ ለመሸጥ ወይም ለመገበያየት

በባለሥልጣኑ በልዩ ሁኔታ የተፈቀደላቸው ሰዎች ወይም የሰዎች ምድብ፤

መሆን አለባቸው፡፡

2/ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ የተመዘገቡ ሰዎችን ዝርዝር ይይዛል፤ እንደአግባቡ በየጊዜው ይከልሳል፡፡

3/ የተመዘገቡ ሰዎች የደንበኞቻቸው ስምምነቶች እና በመካከላቸው እና እርስበርስ የሚደረገው ስምምነቶች ናሙናዎች በአዋጁ አንቀጽ 111 ላይ የተመለከተውን አለመግባባቶችን አፈታት ድንጋጌዎችን ማካተት አለባቸው፡፡

4/ የተመዘገቡ ሰዎች ለካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች፣ ለሠራተኞቻቸው እና ከፍተኛ ተጽዕኖ ያላቸውን ሰዎች በሚመለከተው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ፈቃድ አሰጣጥ እና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 980/2016 በተገለጸው የሥነ ምግባር ደንብ ተገዢ ይሆናሉ፡፡

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን

5/ የዚህ አንቀጽ ማንኛውም ድንጋጌ ቢኖርም በአዋጁ አንቀጽ 61 መሠረት የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ የሆኑ የተመዘገቡ ሰዎች ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት አባል እንዲሆኑ ባለሥልጣኑ እንደመስፈርት ሊያዝ ይችላል።

61. **የዋጋ ተመን ሥርዓት**

1/ የሚከተሉት ለባለሥልጣኑ ቀርቦ ካልጸደቀ በስተቀር የዋጋ ተመን ሥርዓቱ ወደ ሥራ መግባት አይችልም፡-

ሀ) የዋጋ ተመን ሥርዓቱ ገለጻ፤

ለ) አንድ ተጫባጭ ግብይት እንዴት እንደሚከናወን የሚያሳይ ገለጻ፤

ሐ) ስለሰነደ ሙዓለ ንዋዮች እና ለሽያጭ ስለቀረቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪ መረጃ ለተሳታፊዎች የማቅረብ ሥነ-ሥርዓቶች፤

መ) በዋጋ ተመን ሥርዓቱ እና ስልጣን በተሰጠው የማዕከላዊ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት ወይም ፈቃድ ባለው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪ እና ፈጻሚ ኩባንያ መካከል ያለውን ትስስር መግለጫ፤

ሠ) የድህረ-ግብይት መረጃ ህትመት እና ግብይትን ስልጣን ለተሰጠው የማዕከላዊ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት ወይም ለተፈቀደለት የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ሪፖርት የማድረግ ዝግጅት መግለጫ፤

ረ) ቢያንስ የሚከተሉትን የሚዘረዝሩ ውስጠ-ደንቦችና ሥነ-ሥርዓቶች፡-

i) አንድ ሰው በዋጋ ተመን ሥርዓቱ ውስጥ ሊሳተፍ የሚችለው እንዴት እንደሆነ፤
ii) በሥርዓቱ ውስጥ እንዲሳተፍ ተቀባይነትን ያገኘ ሰው የዋጋ ተመን እንዴት ይፋ እንደሚያደርግ፤
iii) በሥርዓቱ ውስጥ ለመሳተፍ ተቀባይነትን ያገኘ አንድ ሰው የሌሎች ተሳታፊዎችን የዋጋ ተመን እንዴት ሊመለከትና በአንድ ይፋ በተደረገ ዋጋ ተቃራኒ ወገን ሆኖ እንዴት መሳተፍ እንደሚችል፤
iv) አንድ ተሳታፊ ይፋ የተደረገን የዋጋ ተመን ለማየት፣ ለማስገባት፣ ለመፈጸም እና ለመክፈል የሚፈቅዱ መብቶችና ኀላፊነቶች፤
v) የሰነደ ሙዓለ ንዋይ የዋጋ ተመን ሥርዓት የሚቋረጥበት ምክንያቶች እና ሥነ-ሥርዓቶች፤እና
vi) የዋጋ ተመን ሥርዓቱን ማቅረቢያ መስፈርቶች እና የተመዘገበ ተሳታፊ በዋጋ ተመን ሥርዓቱ ከመሳተፍ እንዲሰረዝ ሊያበቁ የሚችሉ ምክንያቶች እና ሥነ-ሥርዓቶች።

2/ አመልካቹ ከዋጋ ተመን ሥርዓቱ ጋር በተገናኘ የሚከተሉትን ሰነዶች ማቅረብ አለበት፡-

ሀ) በዋጋ ተመን ሥርዓቱ በተመዘገቡ ሰዎች መካከል እና እርስበርስ የሚደረገ ስምምነት ናሙና ቅጂ፤

ለ) በዋጋ ተመን ሥርዓቱ አከናዋኝ እና በማንኛውም የሦስተኛ ወገን አገልግሎት ሰጪ መካከል የተደረገ ስምምነት ቅጂ፤እና

ሐ) የዋጋ ተመን ሥርዓቱ ጋር የተገናኘ የአሠራር ማኑዋል፡፡

3/ ለገበያ ክትትል እና ቅኝት ዓላማ ሲባል ባለሥልጣኑ ባለው ስልጣን የዋጋ ተመን ሥርዓቱን ያያል፡፡

62. **<u>ስለክፍያ ማጣራትና መፈጸም</u>**

1/ የግብይቱ ክፍያ ማጣራትና መፈጸም ሥርዓት ለተቃራኒው ወገን ተገልጾ ተቃራኒ ወገኑ ካልተስማማባቸው በስተቀር ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ የተደረጉ ግብይቶች መፈጸም አይችሉም፡፡

2/ ያልተማከለ ጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ግብይት ክፍያ ማጣራትና መፈጸም የሚከናወነው በባለሥልጣኑ ስልጣን በተሰጠው ማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት ወይም ፈቃድ በተሰጠው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ በኩል መሆን አለበት፡፡

3/ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ግብይቶችን ክፍያ ለማጣራትና ለመፈጸም ተገቢ የዋስትና ፈንድ ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4/ ስልጣን የተሰጠው ማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት ወይም ፈቃድ ያለው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ በታተመው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ርክብክብ አለመፈጸም ስለሚያስከትለው ውጤት ደንቦች ቢኖሩትም ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያው የክፍያ ማጣራት እና መፈጸም ሥርዓቱ ፈጣን፣ ትክክለኛ እና ግልፅ መሆኑን ማረጋገጥ እና ቢያንስ የሚከተሉትን የሚገልጽ መሆን አለበት፡-

ሀ) ማጣራት የሚፈጸምበት ቀን፤

ለ) የሰነደ ሙዓለ ንዋዩ ርክክብ የሚፈጸምበት ቀን፤ እና

ሐ) ጥሬ ገንዘብ የሚከፈልበት ቀን፡፡

63. **<u>ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ለግብይት ብቁ የሆኑ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች</u>**

1/ አንድ የተመዘገበ ሰው ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ መግዛት ወይም መሸጥ ወይም የግዢ ወይም የሽያጭ ተመን ማቅረብ የሚችለው ፈቃድ በተሰጠው በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ላይ ግብይት በማይደረግባቸው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ላይ ብቻ ነው፡፡

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ላይ የተሸጠ፣ የተገዛ ወይም የተላለፈ ትልቅ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ስብስብ ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ግብይት ሊደረግበት ይችላል፡፡

3/ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከቱት ትላልቅ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ላይ አሰራር ያወጣል እንዲሁም በዚህ አሰራር ላይ የሚደረጉ ማናቸውም ማሻሻያ አስገዳጅ ከመሆኑ ወይም ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በባለሥልጣኑ መጽደቅ አለበት፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግስት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ላይ ግብይት ሊደረግባቸው ይችላል፡፡

## 64. ስለውሎች

1/ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ መልሶ የመግዛት ውልን ጨምሮ የተዛማጅ ውሎች ወይም የተዛማጆች ወይም ተገቢነት ያለው ውልን የመግዛት፣የመሸጥ ወይም የመገበያየት ውስጥ-ደንቦች እና ሥነ-ሥርዓቶች ሊኖሩት የሚገባ ሲሆን እንደነዚህ ያሉ ውስጥ-ደንቦች እና ሥነ-ሥርዓቶች እና ማሻሻያዎች ከመደረጉ እና ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በባለሥልጣኑ መጽደቅ አለባቸው።

2/ ማንኛውም ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ላይ የሚገዛ ወይም የሚሸጥ ውል ትክክለኛ ዋጋ እንዲወጣለት በሚያስችል መንገድ መዘጋጀት እና ውጤታማ የሆኑ የክፍያ ሁኔታዎች ሊኖሩት ይገባል።

## 65. ከዋጋ ተመን ሥርዓቱ በፊት ስለሚፈለጉ መረጃዎች

1/ አንድ የተመዘገበ ሰው የሰነደ ሙዓለ ንዋዩ በአዋጁ ወይም በባለሥልጣኑ በወጣ መመሪያ በባለሥልጣኑ የተመዘገበ ወይም ከምዝገባ ነጻ የተደረገ ካልሆነ በስተቀር በዋጋ ተመን ሥርዓቱ የአንድን ሰነደ ሙዓለ ንዋይ የዋጋ ተመን ማቅረብ አይችልም።

2/ የተመዘገበ ሰው  እንደአግባቡ በመዝገቦቹ የሚከተሉት ሰነዶች ሊኖሩት ይገባል፦

ሀ) በተገቢው የባለሥልጣኑ መመሪያ መሰረት የጸደቀ ደንበኛ ሳቢ መግለጫ ወይም ከሰነደ ሙዓለ ንዋዩ ጋር በተገናኘ አግባብነት ያለው መረጃ ሰጪ ሰነድ የጽሑፍ ቅጂ፤

ለ) ለባለሥልጣኑ ገቢ የተደረገ የቅርብ ጊዜ መደበኛ እና ወቅታዊ ሪፖርት ቅጂ፤እና

ሐ) ለባለሥልጣኑ ገቢ የተደረገ የቅርብ ጊዜ ዓመታዊ ሪፖርት ቅጂ።

3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በመንግስት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

## 66. ግብይቶችን ይፋ ስለማድረግ

1/ በዋጋ ተመን ሥርዓቱ ውስጥ የተፈጸሙ ሁሉም ግብይቶች፦

ሀ) ግብይቱ የተፈፀመበት የስራ ቀን ከማብቃቱ በፊት ለህዝብ ይፋ መደረግ፣ እና

ለ) ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ፈቃድ ማመልከቻ በቀረበበት ጊዜ ባለው ተገቢው የግብይት ሪፖርት ሥርዓት እና ከዛም በኋላ በባለሥልጣኑ ጸድቆ በሚሻሻለው መሠረት ሪፖርት መደረግ፤

አለባቸው።

2/ የተፈጸሙ ግብይቶች ተገቢው ዝርዝር ዋጋ፣ መጠን፣ ግብይቱ የተፈጸመበትን ቀንና ሰዓት ማካተት አለበት።

**67. <u>ክፍያዎችን ይፋ ስለማድረግ</u>**

1/ አንድ የተመዘገበ ሰው አንድ ግብይት ከማከናወን ጋር የሚገናኙ ልዩ ልዩ ክፍያዎች ለደንበኛው ተገልጸው ካልተብራሩና ደንበኛው በክፍያዎቹ ካልተስማማ በስተቀር አንድን ግብይት ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ መፈጸም አይችልም።

2/ የግብይት ክፍያዎች በማረጋገጫ ደረሰኝ መልክ እና ግልጽ እና ለመረዳት በሚያስችል መልኩ መቅረብ አለባቸው።

**68. <u>ቀጣይነት ስላላቸው ግዴታዎች</u>**

1/ ፈቃድ ያለው ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች አክብሮ የሚሠራ ስለመሆኑ በአመታዊ የሕግ አክባሪነት ሪፖርት ውስጥ አካቶ ወይም ባለሥልጣኑ በሚወስነው መሰረት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት።

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን መረጃዎች በተደጋጋሚ በባለሥልጣኑ በሚጠይቀው አቀራረብ እና ቅጽ መሠረት የክትትል ዝግጅት አካል አድርጎ ይጠይቃል፡-

ሀ) ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ላይ ያሉ ግብይቶች እና ተግባራት ሪፖርቶች፤

ለ) በእያንዳንዱ ላይ ምክንያቶችን ወይም ሁኔታዎችን ጨምሮ የተመዘገቡ ሰዎች ላይ የሚደረጉ ማናቸውንም ለውጦች፣ መሰረዝ ወይም መታገድን የሚመለከት ዝርዝር መረጃ፤ እና

ሐ) የተጠረጠረ የተከለከሉ የግብይት ተግባራትን ወይም የሚመለከተውን የሥነ ምግባር ደንብ መጣስ።

3/ ፈቃድ ያለው ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 56 በተቀመጠው መሠረት የሂሳብ መግለጫዎችንና ሪፖርቶችን አዘጋጅቶ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት።

**69. <u>ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ፈቃድ ስለመሰረዝ ወይም መመለስ</u>**

1/ ባለሥልጣኑ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱት ግዴታዎች ወይም ከአዋጁ የሚመነጩ ግዴታዎች ወይም ሌሎች ተዛማጅ መመሪያዎች ያልተከበሩ መሆኑን ሲወስን የአዋጁ አግባብነት ያለውን ድንጋጌዎች በተከተለ መልኩ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ፈቃድ ሊሰርዝ ይችላል።

2/ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ፈቃድ በገዛ ፈቃድ ለመመለስ ለባለሥልጣኑ ማመልከቻ በማቅረብ ሊመለስ ይችላል።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ለባለሥልጣኑ የቀረበ ማመልከቻ፡-

ሀ) የመመለስ እቅዱ ከሚጸናበት ቀን ቢያንስ ከሶስት (3) ወራት በፊት መቅረብ፤ እና

ለ) የዳይሬክተሮች ቦርድ ፈቃድ ለመመለስ ያጸደቀውን ውሳኔ እና ከገበያ ለመውጣት በዳይሬክተሮች ቦርድ የተወሰነው ውሳኔ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የጸደቀበት ልዩ ውሳኔን ማካተት፤

አለበት።

4/ ፈቃድ መመለስ ከሚጸናበት ቀን ጀምሮ ፈቃዱን በመለሰ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ለመገበያየት አይፈቀድም።

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

70. **መስፈርቶችን በጊዜያዊነት ስለመተው ወይም መቀነስ**

ባለሥልጣኑ የካፒታል ገበያውን እድገት እና የተሳታፊዎችን ዝግጁነት እና አቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት አስቀድሞ በዳይሬክተሮች ቦርድ በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት በዚህ መመሪያ የተደነገጉትን ማናቸውንም መስፈርቶች ለጊዜው ሊቀንስ ወይም ሊተው ይችላል፡፡

71. **ተፈጻሚነት የማይኖራቸው መመርያዎች**

ይህን መመሪያ የሚቃረን ሌላ ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

72. **መመሪያው የሚጸናበት ቀን**

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ከተመዘገበበት እና በባለሥልጣኑ ይፋዊ ድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ፣ ሐምሌ 9 ቀን 2016 ዓ.ም

ዶ/ር ብሩክ ታዬ

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን

ዋና ዳይሬክተር